# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 264 ግንቦት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - ዳኜ አበራ

# ሀገራዊ የጋራ እሴቶች አሚጦ መጠቀም እንደሚገባ ተጠቆመ

- ሦስተኛው የኢፕድ የውይይት መድረክ በሐረር ከተማ ተካሂዷል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረር፡- በኢትዮጵያ ከትውልድ ወደትውልድ የተላለፉና ሀገርን በአንድነት ያስቀጠሉ የጋራ እሴቶችን አሚጦ መጠቀም እንደሚገባ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የተሳተፉ እንግዶች ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች" በሚል መሪ ሃሳብ በክልል ከተሞች እያካሄደው ያለው ተከታታይ የውይይት መድረክ አካል የሆነውና በኢትዮጵያ የጋራ እሴቶች ዙሪያ ትኩረቱን ያደረገው ሦስተኛው የውይይት መድረክ በትናንትናው እለት በሐረር ከተማ ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱለም፣ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ፣ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት የሥራ

ሀገራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# በ2030 የተቀመጡ ግቦችን በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢ.ኤ.አ በ2030 የተቀመጡ የዘላቂ ልማት ግቦችን በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትናንትናው ዕለት ኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከተቀበለች ጊዜ ጀምሮ ለሁለተኛ ጊዜ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈጻጸም ግምገማ ተካሂዷል፡፡ የግምገማው አላማ የከፍተኛ ደረጃ የፖለቲካ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍና እንደ ሀገር ዘላቂ ልማት ግቦችን አስመልክቶ ሪፖርት ለማቅረብ የሚያግዝ አንዱ የዝግጅት አካል መሆኑ ተገልጿል፡፡

በግምገማው መድረክ ላይ የተገኙት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ እንደገለጹት፤ እንደ ማንኛውም ሀገር ወደ ኋላ የቀሩብንን የዘላቂ ልማት ግብ

በ2030 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ፍጹም አሰፋ






# ባለስልጣኑ በዓመት እስከ 54ሺ የውሃ ቆጣሪዎችን ለመቁረጥ ተገድጃለሁ አለ

- 100ሺ ደንበኞች የሚጠበቅባቸውን አይከፍሉም

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በዓመት እስከ 54ሺ የሚደርሱ የውሃ ቆጣሪዎችን ለመቁረጥ እየተገደደ ሲሆን፤ ከ100ሺ በላይ ደንበኞች ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ለመክፈል ዝግጁ አለመሆናቸውን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የውሃ ደንበኞች ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሞገስ አርጋው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ደርጅት እንደገለፁት፤ ባለስልጣኑ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ቢሆንም ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉበትም ጠቁመዋል። በተለይም ግብዓቶች የሚገቡት ከውጭ ሀገር ሲሆን፤ ለዚህም ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ እጥረት መኖሩን አስገንዝበዋል። ከዚህ በተጨማሪ የውሃ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችና አልፎ አልፎ የሚስተዋሉ ስርቆቶች መኖራቸውን አስረድተዋል።

እንደ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ገለፃ፤ ባለስልጣኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ቢሆንም ደንበኞች ግን የሚጠበቅባቸውን እየተወጡ አለመሆኑንም ጠቁመዋል። በየዓመቱ ከ10ሺ እስከ 15ሺ የውሃ ቆጣሪዎች የሚቀጠሉ ሲሆን ደንበኞችም ተጠቃሚ እየሆኑ ቢሆንም ቁጥራቸው ከ100ሺ በላይ ደንበኞች ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት



የተጠቀሙትን ለመክፈል ዝግጁ ያልሆኑ ናቸው።

እንደ አቶ ሞገስ ማብራሪያ፤ እስከ 2010 ዓ.ም የነበሩት 42 የመሰብሰቢያ ማዕከላት በአሁኑ ወቅት ወደ 350 አድገዋል። አገልግሎት አሰጣጡም ኋላቀር ነው የሚል ወቀሳ ነበር። ሆኖም ለክፍያ ይሰለፉ የነበሩትን ጫና ለማቃለል በአንድ ዓመት አምስት የክፍያ አማራጮችን ተጀምረዋል። ዊንዶ ሰርቪስ፣ ኢንተርናል ባንኪንግ፣ ሲቢኢ ብር፣ ኢድማርክ አካውንት እና ሞባይል ባንኪንግን ወደ ሥራ አስገብተናል። ሆኖም አሁንም ቢሆን በርካታ ደንበኞች ኃላፊነታቸውን እየተወጡ አይደለም። በዚህም የተነሳ ሥራ ትተን ቆጣሪ ለመቁረጥ እንሄዳለን ብለዋል።

ባለስልጣኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በአማራና አፋር ክልሎች ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የሙያ ድጋፍ መስጠት እንደሚያስፈልግ ተገለጸ

**እፀገነት አክሊሉ**

ደብረብርሃን፡- አሸባሪው ህወሓት በአማራና አፋር ክልሎች ላይ የፈጸመውን ወረራ ተከትሎ በክልሉ ለአእምሯዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች እንዲሁም ማህበረሰቦች ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንና ለዚህም የሚያግዙ ባለሙያዎች በመሰልጠን ላይ እንደሚገኙ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከጤና ሚኒስቴር እንዲሁም ከክልሎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ባዘጋጀው የስልጠና መርሐ ግብር ላይ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አየለች እሸቴ እንዳሉት በአማራና በአፋር ክልሎች በአሸባሪው ህወሓት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴት እህቶቻችን ከደረሰባቸው አሰቃቂ ጉዳት ያገግሙ ዘንድ የአእምሮ ጤናና ስነ ልቦናዊ ድጋፍ ወሳኝነት አለው።

እንደ ወይዘሮ አየለች ገለጻ እነዚህ ወገኖች ወደቀድሞ ህይወታቸው ለመመለስ የሁሉንም አካላት ርብርብ እየጠበቁ ነው፤ ኢትዮጵያውያን ወንድም እህቶቻቸው ከሚያሳዩአቸው አጋርነት በተጨማሪ የሙያው ሰዎች በዚህ መልኩ ሰልጥነው ቢያግዟቸው ህይወታቸው ዳግም ማበብ እንደሚችል ጠቁመዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የጤና ሚኒስቴር ከክልሎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በግጭቶች ምክንያት በግለሰብና ማህበረሰብ ላይ ለተፈጠሩ የአዕምሮ ጤና፣ የስነልቦና እና ማህበራዊ ችግሮች የተቀናጀ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የጋራ እቅድ አዘጋጅተው እየሰሩ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ አየለች ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መገባቱ ደግሞ በጣም አስደሳችና የወገኖቻችንንም ሕይወት በአጭር ጊዜ ወደነበረበት እንዲመለስ የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል።



ወይዘሮ አየለች እሸቴ

በዚህ የተቀናጀ የአዕምሮ ጤና እና የስነልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ ምላሽ ሰጪ ዕቅድ ከተካተቱ ተግባራት መካከል በዘርፉ የሚታየውን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመቅረፍ የሚያስችል የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ክልሎች ስልጠናውን እስከ ታችኛው መዋቅር ተደራሽ እንዲያደርጉና ለተጎጅው ማህበረሰብ የሚፈለገውን የአዕምሮ ጤና፣ የስነልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማስቻል መሆኑን ገልጸዋል።

ቀደም ሲል በአዕምሮ ጤና፣ የስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና በጤና ሚኒስቴርና በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከየካቲት 7 እስከ የካቲት 11 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ 270 ሰልጣኞች መስጠቱን አስታውሰው አሁንም በጦርነት በጣም ከተጎዱ 4 ዞኖች ከዋግኽምራ፣ ከሰሜን ወሎ፣ ከደቡብ ወሎ እና ከሰሜን ሸዋ የተውጣጡ 1ሺ 200 ሰልጣኞችን የማሰልጠን ሥራ ከግንቦት 22 እስከ 26ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እንደሚከናወን ተናግረዋል።

የባለሙያዎች ስልጠና ዓላማው የስነልቦና፣ የማህበራዊና የአዕምሮ ጤና ድጋፍ ምላሽ አሰጣጥ ላይ የማህበራዊ ዘርፍ ሠራተኞች፣ የጤና ባለሙያዎችና የትምህርት ሴክተር ባለሙያዎችን አቅም በማጎልበት በግጭትና በተለያዩ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች በእውቀት ላይ የተመሰረተ የስነልቦና ፣ የማህበራዊና የአዕምሮ ጤና ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ማስቻል መሆኑንም ጨምረው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሳይ ሀይሉ እንዳሉት በአገራችን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ተከስቷል፤ በዚህም ህጻናት ሴቶች እንዲሁም አዛውንቶች የችግሩ ሰለባ ሆነዋል ብለዋል።

ጦርነቱን ተከትሎ በተፈጠሩ ጾታዊ ጥቃቶች በማህበረሰብ ደረጃ አእምሯዊ ጤናና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ተከስተዋል ፤ እነዚህን ቀውሶች ለማከም ከፌዴራል ጀምሮ ክልሎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በመተባበር ለባለሙያዎች ስልጠና በመስጠትና በማሰማራት የስነ ልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ እንዲሰጡ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ የስነ ልቦናና የአእምሮ ህክምና በተፈናቃዮች ማቆያ ማዕከላት ፣ በህክምና ቦታዎች እንዲሁም አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች ላሉ ተጎጂዎች እንደሚሰጥም ጠቁመዋል።

ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንጻር ሁሉም ተጎጂዎች ጋር ለመድረስ የተጠናከረ ሥራ እንደሚጠይቅ እንገነዘባለን ያሉት ዳይሬክተሩ ይህንን የተሟላ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሰራሮች ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው ብለዋል ።

መርሐ ግብሩ የፌዴራልና፤ ክልልና ዞን ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች እና የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በተገኙበት በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረብርሃን ከተማ የተከፈተ ሲሆን ከየዞኑ የተውጣጡ ባለሙያዎች በሰቆጣ፤ በኮምቦልቻ፤ ወልዲያና ደብረብርሃን የተለያዩ ስልጠና ማዕከላት በእያንዳንዱ ማዕከላት 300 ባለሙያዎች በድምሩ ከ1ሺ 200 በላይ ሰልጣኞች እንደሚሳተፉበት ይጠበቃል።



የኦሮሞና የሲዳማ ህዝብ የሰላም ኮንፈረንስ በሃዋሳ ከተማ ተካሂዷል፡፡

# የሲዳማና የኦሮሞ ህዝብን ለማጋጨት መታገል ለድካም ይዳርግ እንደሆን እንጂ አይሳካም

## - አቶ አለማየሁ ጢሞቴዎስ

አዲስ አበባ፡- የሲዳማና የኦሮሞን ህዝብ ለማጋጨት መታገል ለድካም ይዳርግ እንደሆን እንጂ አይሳካም ሲሉ የሲዳማ ክልል ሰላምና ደህንነት ቢሮ ኃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቴዎስ ተናገሩ፡፡

የኦሮሞና የሲዳማ ህዝብ የሰላም ኮንፈረንስ በሃዋሳ ከተማ ተካሂዷል፡፡

በኮንፈረንሱ ንግግር ያደረጉት የሲዳማ ክልል ሰላምና ደህንነት ቢሮ ኃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቴዎስ የሲዳማና የኦሮሞ ህዝብ አንድነት አሁን የተጀመረ ሳይሆን በተፈጥሮ የታደለ አብሮ በመኖር እሴት የተገመደ ነው ብለዋል፡፡

ድንበር ባሉ ወረዳዎች የሚከሰተው ግጭት የተፈጥሮ የፍላጎት አለመግባባት እንጂ የሁለቱን ህዝብ ተቃርኖ የሚያሳይ አለመሆኑንም አመላክተዋል።

ሲዳማና ኦሮሞ 90 በመቶ ድንበር ይጋራሉ ያሉት አቶ አለማየሁ ይህ ህዝብ እርስ በራሱ ተጋጭቶ አያውቅም፤ ነገር ግን ችግሮች በድንበር ሁልጊዜም ይከሰታሉና የሚከሰቱ ችግሮችን በበሰለ አይን ማየት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

የምዕራብ አርሲ ዞን አስተዳዳሪ አቶ አህመድ ሀጂ በበኩላቸው የግጭቶቹ መንስኤ ድንበር መገፋፋትና የግጦሽና ሌሎችም የግለሰቦች ግጭቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በትግሉ ወቅት አብሮ ትልቅ ዋጋን የከፈለ፣ ተፈጥሮ ያስተሳሰረውና ተለያይቶ መኖር የማይችለው የኦሮሞና የሲዳማ ህዝብ በምንም ምክንያት የከረረ ግጭት ውስጥ አይገባም በመሆኑም የሚፈጠሩ ትናንሽ ችግሮችን ቀድሞ ማስወገድ ያስፈልጋል ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሀይሌ ጉርሜሳ በድንበር አካባቢ በተደጋጋሚ ግጭቶች ተከስተው እንደነበር አስታውሰው፣ በሀገር ሽማግሌዎች የዳበረ ግጭት የመፍታት ልምድ በእርቅ መፈታታቸውን ገልፀዋል፡፡

በቅርብም የተከሰተው ግጭት ከዚህ የበለጠ ባለመሆኑ በእርቅ መፈታት የሚችል መሆኑን ነው የተናገሩት።

ነገር ግን በድንበር አካባቢ የሚከሰቱ ችግሮችን ምክንያት በማድረግ ሁለቱን ህዝብ ለማራራቅ የሚሰሩ አካላት እንዳሉ ማህበረሰቡ በመገንዘብ፣ የሚያጋጩ ነገሮች ሲከሰቱ በዳበረው የእርቅ ስነስርዓት ችግሮችን መፍታት እንደሚገባም ማስገንዘባቸውን ፋና ዘግቧል።

በቅርቡ በሲዳማና ምዕራብ አርሲ ወረዳዎች መካከል የተከሰተው ችግር አሁን ላይ መፈታቱን እና ችግሩን ያባባሱ አካላትም በህግ እየተጠየቁ መሆናቸው ተመላክቷል።

# ኢትዮጵያ የማዕድን ቋት እያደራጀች ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የማዕድ ሀብቷን በአንድ ቋት መዝግቦ ለማስቀመጥና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማዋል የምትገለገልበት የማዕድን ዳታቤዝ ፕሮጀክት ቀርፃ እየተንቀሳቀሰች መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

አፍሪካ ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማዕድን ዘርፍ የተሳካ ሥራ የሠሩትን ሀገራት ፈለግ በመከተል የዳታ ቤዝ ፕሮጀክት ተቀርፆ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደተገባ እና ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ፕላን ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱን የዓለም ባንክም በሃሳብ ደረጃ መቀበሉን የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ኢንጅነር ታከለ ኡማ ገልፀዋል፡፡

የማዕድን ዳታቤዝ ፕሮጀክቱ 200 ሚሊዮን ዶላር እንደሚፈጅና እንደ ኢትዮጵያ ምድር በማዕድን ሀብት የበለፀገ እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ መሸከም በሚችሉ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ባላቸው ማዕድናት የተሞላ ምድር ላላቸው ሀገራት አስፈላጊ እንደሆነ ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

የማዕድን ፍለጋ በዓመታት የሚቆጠር ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ሥራውን ለመምራት አስቸጋሪ ነው ያሉት ሚኒስትሩ የማዕድን ዳታቤዝ ሲኖር እንደአጠቃላይ የኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የሚገኙ ማዕድናትን በማጥናት እያንዳንዱ ሃብት በምን ዓይነትና መጠን እንዳለ መረጃ ስለሚኖር ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ኢንቨስትመንት ሲመጣ በማዕድን ፍለጋ የሚባክን ጊዜ ሳይኖር በቀጥታ ወደ ምርት ስለሚገባ ለኢኮኖሚው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የማዕድን ዳታቤዝ ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ውድ ማዕድናትን ያሉበትን ቦታ እና መጠን ለማወቅና ለመጠቀም ያስችላል፡፡ ከዚህ ፀጋ መጠቀም እንዲያስችላቸውም ክልሎች የማዕድን ኮርፖሬሽን እንዲያደራጁ እየረዳናቸው ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ የመጣችበት መንገድ ከፍተኛ የእሳቤ ችግርና ሳንካዎች የነበሩበት ነው ያሉት ኢንጅነር ታከለ፤ የማዕድን ዘርፉ የጠራ ዕይታ ያልነበረበት እና ማዕድንን እንደ ፀጋ ከመቁጠር ይልቅ እንደግጭት መንስዔ አድርጎ የሚመለከት ሆኖ ቆይቷል ብለው በዚህም ምክንያት ከፍተኛ እና ጥራት ያለው የማዕድ ሀብት እያለን እንደሌለን ሆነን ቆይተናል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

እንደ ኢንጅነር ታከለ ገለፃ፤ ችግሩን ለመፍታት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሪፎርም በተወሰዱ እርምጃዎች በማዕድን ዘርፉ መነቃቃት ታይቷል፡፡ በተለይ ባለፉት ሦስት ዓመታት ማዕድን የኢትዮጵያ ብልፅግና ዕቅድን ከሚያሳኩ የብዝኃ ኢኮኖሚ ምሶሶዎች አንዱ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሆኗል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሀገሪቱ የሚገኙ የማዕድን ሀብቶችን በብዛት፣ በጥራት እና በዓይነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለሀገራችን ኢኮኖሚ የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ ዋና ዓላማው እንደሆነ ተናግረው ማዕድናት ጥቅም ላይ ሲውሉ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ እንዲሆንም ሚኒስትሩ አስረድተዋል፡፡

እንደ ኢንጅነር ታከለ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ ማዕድን ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ ሚዛኑን ያልጠበቀ ትርክት የነበረ፡፡ ይህ የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ለውጭ ገበያ ከማቅረብ ከመገደቡም በላይ ያሏትን ፀጋዎች እንዳትመረምር ጋርዷት ቆይቷል፡፡

ለዚህ እንደማስረጃ የኢትዮጵያን የከሰል ማዕድን ምርት በውጭ ሀገራት ኩባንያዎች ተመርምሮ የተገኘው ዕውነተኛ ያልሆነ ውጤት አሁን ወደተለያዩ ሀገራት ተልኮ ትክክለኛ የከሰል ይዘቱ እንደታወቀ ኢንጅነሩ ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ የድንጋይ ከሰል ጥራት እንደሚጎድለውና የእርጥበት መጠን ከፍተኛ መሆን እና አሸ መጠኑ ትልቅ መሆኑ ሲነገር እንደነበር የገለፁት ኢንጅነር ታከለ ማዕድኑ ወደቱርክ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ቻይና ናሙናዎችን በመላክ በተደረገው ማጣራት ከውጭ ከምናስገባቸው የድንጋይ ከሰል ምርቶች በላቀ ደረጃ የሚገኝ የድንጋይ ከሰል በሀገራችን እንደሚገኝ ተረጋግጧል ብለዋል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የድንጋይ ከሰል ምርቶች 5 ሺህ የማቃጠል አቅም ያላቸው ሲሆኑ የኢትዮጵያ የድንጋይ ከሰል የማቃጠል አቅም 6 ሺህ እና ከዚያ በላይ መሆኑ በመረጋገጡ ለሲሚንቶ ምርት እንደግብዓት ለመጠቀም ከፍተኛ መነቃቃት መታየቱንና ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ከውጭ የሚገቡ የድንጋይ ከሰል ምርቶችን ለማስቀረት ርብርብ እየተደረገ እንደሆነ ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡፡፡

በድንጋይ ከሰል መስክ የታየውን የራስን ፀጋ የመጠቀምና የማወቅ ተግባር በማስቀጠል ሌሎች ሥራዎችም እንደሚሠሩ ሚኒስትሩ ተናግረው፤ ማዕድናችንን እንዳናይ ፀጋችንን እንዳንጠቀም የተነዛው ዓለም አቀፍ ትርክትን ማሸነፍ የምንችለው በመሥራት ብቻ ነው ብለዋል፡፡



የመስኖ ልማት መሬት ዝግጅት



በሰብል የተሸፈነ የመስኖ መሬት

# የመስኖ ልማትን ከ400ሺህ ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ለማሳደግ እየተሰራ ነው

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የመስኖ ልማት ሥራን ከ400ሺህ ወደ አንደ ሚሊዮን ሄክታር ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የተፋሰስ ልማት አገር አቀፍ አስተባባሪ ዶክተር ዳንኤል ሙለታ እንደገለጹት፣ ባለፈው ዓመት በመስኖ በ400ሺህ ሄክታር ላይ ለምቷል፡፡ይህንኑ ተሞክሮ በመውሰድም የመስኖ ልማት ሥራን ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ለማሳደግ እየተሰራ ነው፡፡

እንደ አገር የመስኖ ፕሮጀክቶችን ለማበራከት መታቀዱን የገለጹት ዶክተር ዳንኤል፣ የመስኖ ልማት ሥራን ከ400ሺህ ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ከማድረግ በተጨማሪም በአምስት ክልሎች ብቻ (አማራ፤ኦሮሚያ፤አፋር፤ደቡብ፣ሲዳማ ) ተወስኖ ሲሰራ የነበረውን የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ትግበራ በሌሎች ክልሎችም ለማስፋትና ተደራሽ ለማድረግ ተያይዞ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የስንዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሥራ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሚሆን የጠቀሱት ዶክተር ዳንኤል፣ የፕሮጀክት ትግበራው ለውጥ የታየበት በመሆኑ በሁሉም ክልሎችና በሌሎችም ሰብሎች ላይ የፕሮጀክት ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለጻ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በአምስት ክልሎች የተጀመረው የመስኖ ልማት ሥራን በቀጣይ በሌሎች ክልሎች በማስፋፋት ሂደት እንደታቀደ ጠቁመው፣ በሂደቱ በቀጣዩ ዓመት የሶማሌ ክልልን ጨምሮ በከፊል የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል፣ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በሌሎች አካባቢዎች ላይ በማስፋት ምርታማነቱን ለማሳደግ ያለመ ሥራ እየተሰራ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግና አገራዊ የግብርና ምርት ፍጆታን በማሳደግ በአገር ውስጥ የግብርና ምርት ከመሸፈን አንጻር ካለው ፋይዳ ጋር ተያይዞም በሁሉም ክልሎች ለመተግበር በእቅድ መያዙን ተናግረዋል፡፡የመስኖ ልማቱን የማስፋፋት ሥራው እንደ አገር እየተሰራበት ነው ብለዋል፡፡

የበጋ መስኖና በክረምት ወቅት ስንዴን በማልማት ከኢትዮጵያ አልፎ የጎረቤት አገራትን የስንዴ ምርት እጥረት ለመፍታት በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ዶክተሩ ጠቁመዋል።

አክለውም የበጋ መስኖና በክረምቱ ስንዴን በስፋት በማልማት የውጭ ጫናን በመቋቋም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስቀጠልና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥም ዓይነተኛ ሚና ስላለው ሥራው በስፋት ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የነበሩትና በቀጣይ የሚሆኑ አርሶ አደሮች በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ ማሽላ፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማልማትና በማምረት በዓመት ውስጥ ከሁለት እስከ ሦስት ጊዜ ምርት ማምረት የሚያስችላቸው እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

## የኦሮሚያ ክልል ከ 4 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ በማሰራጨት ላይ መሆኑን አስታወቀ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮ መኸር እርሻን ጨምሮ 4 ነጥብ 785 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ በማሰራጨት ላይ እንደሚገኝ አስታወቀ ፡፡ ክልሉ ከሚያስፈልገው ማዳበሪያ ፍላጎት 76 በመቶ ኩንታል ማዳበሪያ መቅረቡን ገልጿል፡፡

በክልሉ ግብርና ቢሮ ፍላጎትና ምርት ማሳደግ ግብዓት ዳይሬክተር አቶ ታከለ ቁሩንዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ክልሉ ለበጋ መስኖ፣ በልግና መኸር እርሻ ለአርሶ አደሩ የሚያስፈልገውን ማዳበሪያ በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡ እስከ አሁን በተሰራው ሥራ ክልሉ የሚያፈልገውን የማዳበሪያ ፍላጎት 76 በመቶውን በእጁ ማስገባቱን ገልጸዋል፡፡

አቶ ታከለ የክልሉ አርሶ አደር 8 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፣ ፍላጎቱን ለማሟላት ከግብርና ሚኒስቴር በሚፈቀድ ግዥ ፣መጋዘን ውስጥ ካለው ማዳበሪያና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ በማዘጋጀት ምለሽ ለመስጠት እየተሰራበት ነው፡፡ በሁሉም ዞኖች አስፈላጊውን የማዳበሪያ ዝግጅትና ስርጭት እየተካሄደ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ታከለ ገለጻ በግብርና ሚኒስቴር ከተፈቀደላቸው 5 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ 4 ሚሊዮን 785 ሺህ 976 ኩንታል ማዳበሪያ በክልሉ ማዳበሪያ የሚያሰራጩ መሰረታዊ ማህበራትና ዩኒየኖች መጋዘን ደርሷል ፡፡ እስከ አሁን ድረስ በተሰራው ሥራ በጋ መስኖ ፣ በልግና ለቀጣይ መኸር እርሻ በድምሩ 2 ነጥብ 042 ሚሊዮን በላይ ማዳበሪያ አርሶ አደሩ እጅ መግባቱን አስታውቀዋል፡፡

ከክልል ጀምሮ የማዳበሪያ ስርጭት የሚካሄደው አርሶ አደሩን ማዕከል ባደረጉ መሠረታዊ ማህበራትና ዩኒየኖች አማካኝነት በተለያዩ ምክንያቶች ለሚከሰቱ የማዳበሪያ እጥረቶች ክልሉ 54 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት ክፍተቱን



አቶ ታከለ ቁሩንዴ

ለመሙላት አቅጣጫ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ነው ፡፡ እስከ አሁን በተሰራው ሥራ 42 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ኮምፖስት ማዳበሪያ መዘጋጀቱን ገልጸዋል ፡፡

ከባለፈው ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር የማዳበሪያ ዋጋ ብዙ ለውጥ እንዳለው የገለጹት አቶ ታከለ አርሶ አደሩ ማዳበሪያ ዋጋ ጨምሯል፣ የለም ተብሎ የሚናፈሰውን የውሸት ወሬ ወደ ጎን በመተው የቀረበለትን ማዳበሪያ ጊዜውን ጠብቆ በመቀበል ሊጠቀምበት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ እጥረት ከመከሰቱ በፊት የኮምፖስት ዝግጅት በመሰራቱ ከመጋዘን የከረመ ማዳበሪያና በግዥ ከሚቀርበው አቅርቦት ጋር ተደምረው የከፋ የማዳበሪያ እጥረት ይከሰታል የሚል ስጋት እንደሌላቸው ገልጸዋል ፡፡

አንድ ሚሊዮን ኩንታል ዘር ለማሰራጨት መታቀዱን ጠቅሰው እስከ አሁን 200 ሺህ 24 ሺህ ኩንታል ዘር ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል ፡፡ በክልሉ ለዘንድሮ የዘር አቅርቦት እጥረት እንደማይኖርም ገልጸዋል፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎች አርሶ አደሩ አስፈላጊውን የግብዓት ዝግጅት እንዲያደርጉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነጻ ለማድረግ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብር ተጀመረ

- በኢትዮጵያ በዓመት ከ17 ሺ በላይ ዜጎች በትምባሆ ጭስ ህይወታቸውን ያጣሉ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነጻ ለማድረግ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብር ተጀመረ። በኢትዮጵያ በዓመት ከ17 ሺ በላይ ዜጎች በትምባሆ ጭስ ህይወታቸውን እንደሚያጡ ተገለጸ።

በዓለም ለ35ኛ በኢትዮጵያ ለ30ኛ ጊዜ “የጸረ ትምባሆ ቀን ለእኛና ለምድራችን ስጋት ነው” በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ትናንት ተከብሯል።

በአዲስ አበባ ሁሉም ክፍለ ከተሞች የተሳተፉበት አዲስ አበባን ከትምባሆ ነጻ የማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ የንቅናቄ ሥራ ተጀምሯል።

የጸረ ትምባሆ ቀን ትናንት በተከበረበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድሃኒት፣ የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትግስት በዳዳ ቀኑን አስመልክቶ እንደገለጹት፤ የትምባሆ ጭስ በሰው ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነው።

ትምባሆ በሰው ልጆች ላይ እያደረሰ ያለው የጤና ጉዳት አሳሳቢ በመሆኑ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት አላማ ያደረገ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፣ የትምባሆ ጭስ ከሌሎች በሽታዎች በበለጠ በሰው ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው። በዓለም በዓመት ስምንት ሚሊዮን ገደማ ሰዎች በትምባሆ ጭስና በእነሱ ምክንያት በተዘዋዋሪ ስምንት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ህይወታቸው ያልፋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1112/2011 በወጣው አዋጅ መሰረት የትምባሆ ምርት የጤና ማስጠንቀቂያና ገላጭ ፅሁፍ ቁጥር 45/2012 ህገ ወጥ የትምባሆ ንግድ ቁጥጥር



ማስወገድ ፕሮቶኮል ለመፈረምና ለማጽደቅ ሂደት ላይ ነው። ህብረተሰቡ ራሱን ከትምባሆ ጭስ መጠበቅ አለበት፣ እኔ አላጨስም ብሎ በዝምታ መመልከት ብቻ ሳይሆን በያገባኛል ስሜት መካከል ያስፈልጋል ብለዋል።

የትምባሆን ጭስ ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዳይሬክተሯ፤ በሕዝብ መዝናኛዎች፣ ሆቴሎች ላይ በሚያጨሱ አካላት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። ሁሉም ህብረተሰብ የትምባሆን ጭስ ለማስቆም 9864 ነጻ የስልክ መስመር በመደወል ጥቆማ ማድረስ መቻል እንዳለበት አሳስበዋል።

እንደ ወይዘሮ ትግስት ገለጻ፤ ባለስልጣኑ ከሚሰራቸው ተግባራት መካከል አንዱ የትምባሆንና አደንዛዥ ዕጽን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነጻ የማድረግ ሥራ ተቀርጾ እየተሰራ ነው።

የዓለም አቀፍ የጸረ ትምባሆ ቀንን ምክንያት በማድረግ ትምህርታዊ የቅስቀሳ ሥራ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር በከተማዋ አምስት የሚደርሱ ክላስተሮችን መሰረት ያደረገ የሶስት ቀን የጸረ ትምባሆና ሱስ ትምህርታዊ ቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርታዊ ቅስቀሳ መካሄድ ጀምሯል።

# ሚኒስቴሩ ሴት የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎችን የማበረታታት ግዴታውን እንደሚወጣ ገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ሴት የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችን የማበረታታት ግዴታውን እንደሚወጣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ሴቶች ማኅበር ትላንትና "ሴቶች በመገናኛ ብዙኃን ያላቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት እንሠራለን" በሚል መሪ ሃሳብ ባዘጋጀው መርሐግብር በዲጂታል ሚዲያ ዘመን ጉልህ ሥራዎችን ላከናወኑ ሴት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ዕውቅና ሰጥቷል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታዋ አለሚቱ ኡመድ እንደገለጹት፤ ሴት ጋዜጠኞች በመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ ከቀን ወደቀን እየተሻሻለ ቢመጣም ሚኒስቴሩ ሴት የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎችን የማበረታታት ግዴታውን በይበልጥ ለመወጣት ዝግጁ ነው።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ሴቶች ማኅበርን የመደገፍና የማበረታታት ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡ በማህበሩ በኩል የሴት ጋዜጠኞች አቅም እንዲጎለብትና በሙያቸው ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ የበኩሉን ጥረት ይወጣል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፤ ሴቶች የማህበረሰቡን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አንቂ ሆነው መቅረብ ይችላሉ። በዚህ ረገድ ጅምሩን ያሳዩ ወጣትና አንጋፋ ሴቶች አሉ። ይህንን ልምድ በማጎልበት በርካታ ሴቶች በመገናኛ ብዙሃኑ ዘርፍ ስኬታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ሁሉም የበኩሉን ጥረት መወጣት ይኖርበታል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከዕውቅና መርሐግብሩ በኋላ ‹‹ዘመነ ዲጂታል ለሴቶች በረከት ወይስ ተግዳሮት›› በሚል ርዕስ ሴት ጋዜጠኞች ውይይት አካሂደዋል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ሴቶች ማኅበር የቦርድ አባል ጋዜጠኛ የሸዋ ማስረሻ ባስተላለፈችው መልዕክት፤ ማህበሩ አድሎአዊና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል ጠንካራ ሴት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች እንዲፈጠሩ ጥረት ያደርጋል። ሚኒስቴሩ የማህበሩን አላማ በመደገፍ የሴቶችን



**አለሚቱ ኡመድ**

አቅም ለማጎልበት መነሳሳቱ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ይወሰዳል።

በሌላ በኩል ዲጂታል ሚዲያው ለሴቶች ይዞ የመጣውን መልካም አጋጣሚ ያህል በርካታ ተግዳሮቶችን ይዞም መምጣቱን የገለፀችው ጋዜጠኛ የሸዋ፤ ለዚህም ሴቶች ዝግጁ እንዲሆኑ ለማስቻል ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑንም አመላክታለች፡፡

የሴቶች ጉዳይ ማርች ስምንት ላይ ብቻ የሚታወስ ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም የዕለት ተዕለት ተግባር አድርጎ በቁምነገር ስለሴቶች የሚያነሱ ጉዳዮችን በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት ያስፈልጋል ብላለች፡፡

በጎ የሰሩትን በማበረታታት ረገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አንጋፋ ሴት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ዕውቅና መሰጠቱ ተገቢ መሆኑን ጋዜጠኛ የሸዋ ተናግራለች።

በመርሐግብሩ በዲጂታል ሚዲያ ላይ የሚሠሩ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ከሲዳማ፣ ሃረሪ፣ አማራና ኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ከድሬዳዋና አዲስ አበባ መስተዳድሮች የተውጣጡ ሴት ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

# የሠዎች መብቶችና ጥቅሞች እንዲከበሩ የሲቪክ ማህበራት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ተጠየቀ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



አዳማ፡- በሕግ የተደነገጉ የሠዎች መብቶችና ጥቅሞች እንዳይጣሱ ሲቪክ ማህበራት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ ከብዙሀን ማህበራትና ፌዴሬሽኖች ጋር በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ግንባታ ዙሪያ አብሮ ለመስራት የሚያስችል ስምምነት በተፈረመበት ወቅት እንደተናገሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሚሠራቸውን ሥራዎች ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ያስፈልገዋል።

ከእነዚህም መካከል በአስፈጻሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፤ ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሠፍን የሲቪክ ማህበራት ተሳትፎ ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛል።

ዶክተር እንዳለ እንደገለጹትም እንደ ሀገር የሠዎችን መብቶችና ጥቅሞች በማስከበር ረገድ አብዛኛውን ኃላፊነትና ተግባር ለመንግሥት የመተው ነገር በስፋት ይስተዋላል። ነገር ግን ነባራዊው ሁኔታ የሚነግረንና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየንም በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ የሲቪክ ማህበራት ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የሲቪክ ማህበራት ለመንግሥት ያልታዩ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በማውጣት፤ ብሎም ክፍተት ያለባቸው የመንግሥት ፖሊሲና ህጎች እንዲስተካከሉ ምክረ ሀሳብ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ፋሲካው ሞላ በበኩላቸው እስካሁን በኢትዮጵያ በተደረጉ አስተዳደራዊ ለውጦች በየደረጃው የተመለሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ቢኖሩም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በማስፈን ረገድ ግን እዚህ ግባ የሚባል ሥራ አልተሠራም። ሲቪክ ማህበራት ደግሞ የሕዝብን ጥቅም የማስጠበቅና የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እሴቶች እንዲጎለብቱ የማድረግ ሕጋዊም ሞራላዊም ግዴታ አለባቸው።

የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ዋነኛ መዳረሻቸው የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው። ለዚህ ደግሞ የመንግሥት አስተዳደርና አሰራር ግልጽነት ያለው ሊሆን ይገባል። ይህን ለመፍጠር ደግሞ ሲቪክ ማህበራት ሁነኛ መንገድ ናቸው።

ለዚህም ሲቪክ ማህበራት ማህበረሰብን የማንቃት፤ መተባበር መቻቻል ያለበት የፖለቲካ ምህዳር እንዲፈጠር የማድረግ፤ በሀገራዊ ጉዳዮች የጋራ መግባባት እንዲፈጠር የመስራት እንዲሁም ሙስና የሚፈጽሙና አስተዳደራዊ ጥፋቶችን የሚሠሩ አካላትን በማስረጃ ማጋለጥ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪ ጥናቶችን በማድረግ የፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብ። እነዚህንም ከወረት በዘለለ በዘላቂነት ማከናወን ይገባል ብለዋል፡፡

አቶ ፋሲካው እንዳሉትም ከዚህ በፊት ሲቪክ ማህበራትን የተመለከቱ ሕጎች የሚያሠሩ አልነበረም፤ ከለውጡ በኋላ ግን ሙሉ ለሙሉ ስለተስተካከሉ ማህበራቱ ያላቸውን አቅም በመጠቀም የሚጠበቅባቸውን ሊወጡ ይገባል። በተለይም ብዙ አባላት ካሏቸው ማህበራት ብዙ የሚጠበቅ ይሆናል።

# ሀገራዊ የጋራ እሴቶች አሚጦ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊዎች፣ ምሁራን፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል ተወካዮች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተዋል።

ለውይይት መነሻ የሚሆን ጽሁፍ ያቀረቡት የሐረሪ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ቅርስ ቢሮ ኃላፊ አቶ ተወለዳ አብዶሽ፣ የሕግ ባለሙያና ጠበቃ አቶ ቀለመወርቅ ሚደቅሳ እንዲሁም ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ ሲሆኑ ጽሁፎቹ የኢትዮጵያውያን የሥነ-ልቦና ውቅርና የጋራ እሴቶች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ነበሩ።

ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንደሀገር ያቆሙባቸው እሴቶች አላቸው ያሉት አቶ ተወለዳ አብዶሽ ናቸው።

አቶ ተወለዳ በጽሁፋቸው ያሉንን የጋራ እሴቶቻችን አጥንተን መጠቀም አለብን ያሉ ሲሆን፤ በተቃራኒው የእኛ ያልሆኑ እሴቶች ደግሞ ማስወገድ አለብን ብለዋል።

ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ለአገር ግንባታ ያላቸው ድርሻ ላቅ ያለ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ተወለዳ፤ እነዚህን እሴቶችንም ለሀገር ግንባታ አሚጠን እንዳልተጠቀምንባቸው አስረድተዋል።

ኢትዮጵያውያን የተመሰረቱባቸውን የጋራ የልቦና ውቅሮችን በመጥቀስና ማሣያዎችን በማንሳት ያብራሩት ሌላኛው ጽሁፍ አቅራቢ አቶ ቀለመወርቅ ሚደቅሳ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ከሁሉም ማዕዘን ያልተቋረጠ ማኅበራዊ እና የንግድ ግንኙነት የነበራቸው፣ አሁንም ያላቸው ወደፊትም የሚኖራቸው ህዝቦች ናቸው ብለዋል።

ማኅበራዊ እሴቶቻቸውም ለተቀረው ዓለም ምሣሌ መሆን የሚችል ነው ያሉት አቶ ቀለመወርቅ፤ ለዚህም በአሁኑ ውቅት የሕግ ከለላ የተሰጠውና መንግሥትም የሚያበረታታው ጉዲፈቻን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ብለዋል።

አርበኝነት ሌላው የኢትዮጵያውያን የጋራ እሴት የሆነ የኢትዮጵያውያን ምልክት መሆኑን ያነሱት ጽሁፍ አቅራቢው፤ ኢትዮጵያውያን ሀገርንና ሕዝብን ከጠላት በመጠበቅ በጋራ ታሪክ እየሠሩና እያጻፉ የመጡ ህዝቦች መሆናቸውንም አንስተዋል።

የሃይማኖት እሴቶችም ቢሆኑ የኢትዮጵያውያን የጋራ መተሳሰሪያ ገመድ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ የቀደምት ሃይማኖቶች መኖሪያና መገኛ መሆኗን ገልጸ ዋል።

ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ በበኩላቸው፣ ሐረር ከተማን እንደተምሳሌት በመጥቀስ "እኛ ኢትዮጵያውያን ለውጭ ጠላት እጅ የማንሰጥ፣ ስልጣኔን የምንወድ እንዲሁም መቻቻል፣ መዋደድና ደግነት መገለጫችን የሆነ፣ የጥንታዊ ቅርሶች መገኛ፣ እንኳን ሰውን አራዊትን ማላመድ የምንችል፣ ጀግኖች ብቻም ሳንሆን ጥበበኞች፣ ችግሮቻችን በራሳችን መፍታት የምንችል ድንቅ ሕዝቦች ነን" ብለዋል።

አንድ ሰው ሙሉ ኢትዮጵያን መጎብኘት በቂ ጊዜ ባይኖረው እንኳን የሀረር ከተማን ቢጎበኝ በቂ ነው ሲሉም ተናግረዋል። አክለውም፣ ሐረር የፍቅርና የመቻቻል ከተማ ናት፤ ኢትዮጵያም እንደዛ የሆነች ሀገር መሆኗንም በማሣያዎች አብራርተዋል።

የፓናል ውይይቱን የመሩት የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ እንደተናገሩት፤ ለዘመናት ተጠብቀው የቆዩት የጋራ ሀገራዊ እሴቶቻችን ተጠብቀው እንዲቆዩ የአባቶች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

እነዚህን ለዘመናት የቆዩ እሴቶቻችን ሊሸረሽሩ የሚችሉ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ጠቅሰው፤ እሴቶቻችን ለመሸርሸር የሚደረጉ ጥረቶች የኢትዮጵያን ህልውና ለማጥፋት ከሚደረግ ጥረት ተለይቶ የሚታዩ አይደሉም ብለዋል።

ትውልዱ ለሀገሩ የሚጠበቅበትን እንዲያበረክት ታሪኩን ሊያውቅ ይገባል፤ መነሻውን ያላወቀ ትውልድ መድረሻውን አያውቅም ያሉት ሚኒስትሩ፤ አንድን ትውልድ ታሪኩን እንዳያውቅ ከተደረገ ከንቱ ትውልድ ሊፈጠር እንደሚችልም አብራርተዋል።

የሰለጠነች፣ ዴሞክራሲ የሰፈነባትና ሰላሟ የተረጋገጠ ሀገር እንድትኖረን ወጣቱ ትውልድ ታሪኩን እንዲያውቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል።

# ባለስልጣኑ በዓመት እስከ 54ሺ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዓመት እስከ 54ሺ ቆጣሪ ቆርጠናል፤ ይህ ትልቅ ፈተና ነው ለሥራችን እንቅፋት እየሆነ ነው።

ደንበኞች የሚከፍሉት የውሃ ታሪፍ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር በጣም ርካሽ ነው ያሉት አቶ ሞገስ፤ ባለስልጣኑ አንድ ሜትር ኪዩብ ውሃ ለማምረት ቀደም ሲል በነበረው ገበያ 30 ብር የሚያወጣ ሲሆን ይህን ውሃ ለደንበኞች የሚያቀርበው ግን 2ብር 40 ሳንቲም ነው። ተቋሙ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እየተጋ ቢሆንም በውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች እየተፈተነ መሆኑንም አብራርተዋል። ጥቂት ደንበኞች ምናልባትም ከ20 እስከ 25 በመቶ ደንበኞች በሚፈጥሩት ችግር ተቋሙ በፋይናንስ እጥረት እንዲፈተንም ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል። በመሆኑም በዚህ ላይ የመገናኛ ብዙሃን የጠራ መረጃ ይዘው ሊያግዙን ይገባል ብለዋል።

ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው፤ ደንበኞቹን የውሃ እና ፍሳሽ ብሎ በሁለት የከፈለ፤ በአሁኑ ወቅት ከውሃ አኳያ ወይንም ውሃ ቆጣሪ በቤታቸው የተገጠመላቸው 600ሺ ደንበኞች አሉት። ከፍሳሽ አኳያ ወይንም በዘመናዊ መንገድ መስመር ተዘርግቶ ፍሳሽ የሚያስወግዱ ደንበኞች ደግሞ 198ሺ በላይ የሚሆኑ ናቸው።

# በ2030 የተቀመጡ ግቦችን በተሻለ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አፈጻጸሞች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት እ.ኤ.አ በ2030 የተቀመጡ ግቦችን ሁሉ በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ እንደ ሀገር ሪፖርት ሊደረግ በመሆኑ አፈጻጸሙን ሕጋዊ ማድረግ፤ ሂደቱ ትክክል ነው? አይደለም? የሚለውን በመለየት ያልተካተተ ካለ እንዲካተት ይደረጋል። የኢትዮጵያ አካሄድ ለዘላቂ ልማት ግቦች ለብቻ እቅድ ማቀድ ሳይሆን የሀገራዊ እቅድ አካል አድርጎ መስራት ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ ላይም የኢትዮጵያ ተሞክሮ ጥሩ ተብሎ ይነሳል ብለዋል። የየትኛውንም ሀገር ልምድ ስንመለከት ከኢትዮጵያ የተሻለ ልምድ ያለው ሀገር አለመኖሩን ገልጸዋል።

ደሃ ተኮር የሆኑ ዘርፎች ላይ በአማካኝ 62 በመቶ የኢትዮጵያ መንግሥት በጀት ይመድባል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይህ ደግሞ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ትልቅ ሚና አለው። በአንዳንድ ሀገሮች ሀገራዊ በጀትና የዘላቂ ልማት በጀት ተነጣጥለው በመበጀታቸው እቅዳቸውን እንዳያሳኩ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነባቸው ተናግረዋል። በኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት እቅዶች ከዋናው የሀገር እቅድ ጋር ተካተው ስለሚሰሩ ጥሩ ውጤት መገኘቱን አብራርተዋል።

ብዙ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ በሆኑ ምክንያቶች ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ተግዳሮቶች የነበሩበት በመሆኑ ለልማት እቅድ አፈጻጸማችን ከፍተኛ ፈተና ነበር። ነገር ግን ዘላቂ የልማት ግቦችን እንደ ራሳችን እቅድ አድርገን በእቅድ ውስጥ አካተን መሄድ በመቻላችን በብዙ አመላካቾች ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል፤ በቀጣይም ክፍተት ያለባቸውን የዘላቂ ልማት እቅዶችን ለማሳካት ትልቅ እገዛ ይኖረዋል ሲሉ ገልጸዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አህመድ ሺዴ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። በተለይ የዘላቂ ለማት ግቦቻችንን መገምገማችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሪፖርት በሚቀርብበት ጊዜ ሀገራችን ለዘላቂ ልማት ቁርጠኛ መሆኗን ያሳያል። ባለፉት አራት ዓመታት ሰፊ የሆነ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሲካሄድ ቆይቷል፤የለውጥ እሳቤዎቹ ወደ አስር ዓመት እቅድ ተቀይረው ተግባራዊ እየሆኑ ይገኛሉ። ይህም ከዘላቂ ልማት ግቦቻችን ጋር የተጣጣመ ነው ብለዋል።

የዘላቂ ልማት ግቦች ሥራ በፌዴራል ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች የአሰራር ሥርዓት ተከትለን እየሰራን በመሆኑ አውንታዊ የኢኮኖሚ ለውጥ እየመጣ ነው።አብዛኛዎቹን የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት የሚያስችል ደረጃ ላይ ነን ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## እያሸነፍን እንሻገራለን፤ እየተሻገርንም እናሸንፋለን!

አገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የአገረ መንግስት ታሪክ ካላቸው ጥቂት የዓለም አገራት ውስጥ አንዷ ናት። በዚህ ረጅም ታሪክ ውስጥም ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች፤ በበጎም ይሁን በመጥፎ ሊጠቀሱ የሚችሉ የሰፊ ታሪክ ባለቤት መሆንም ችላለች። ብዛት ባላቸው ታሪካዊ አጋጣሚዎች ካጋጠሟት ከፍ ያሉ ተግዳሮቶችም የተነሳ አበቃላት ስትባል ቆማ መሄድ ስትችልም ታይታለች።

ለዚህም ህዝቦቿ ለዘመናት ያካበቷቸው ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ እና ማህበራዊ እሴቶችም ወሳኝ ስፍራ አላቸው፤ እነዚህ እሴቶች አገረ መንግስቱ በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲዋቀር እና በየዘመኑ ያጋጠመውን ተግዳሮት አሸንፎ እንዲወጣ፤ አገር እንደ አገር ጸንታ እንድትቆም ወሳኝ አቅም እንደነበሩም ይታመናል።

የአገርን እጣ ፋንታ ከራስ እጣ ፋንታ ጋር አስተሳስሮ ማሰብና ለዚህም እራሱን መስጠት የቻለ ትውልድ በማፍራት ሂደት ውስጥም እነዚህ እሴቶች በዘመናት መካከል የነበራቸው አስተዋጽኦ አገርን እንደ አገር ከመሻገር ባለፈ ስለ አገር ተስፈኛ ትውልድ በመፍጠር ሂደትም የነበራቸው አስተዋጽኦ አልፋና ኦሜጋ ነው።

ሰብዓዊነትን፣ ወንድማማችነትን፣ አብሮነትን፣ ተከባብሮና ተቻችሎ መኖርን መሰረት ያደረጉ እነዚህ አገራዊ እሴቶች በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶችን የልቦና ውቅር ጤናማ እንዲሆን በማድረግ ትውልዶች ከእኔነት በላይ ማህበራዊ ማንነታቸው ጎልቶ እንዲወጣ፤ በዚህም እንዲገሩ ማድረግ አስችሏል።

እነዚህ እሴቶች አገር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን በምትሆንበት ወቅት አገረ መንግስቱ ተንገዳግዶ እንዲቆምና መልሶ እንዲጸና ወሳኝ አቅም የፈጠሩ፤ ህዝባችን እንደ ህዝብ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ በገባችባቸው ወቅቶችም ፈተናዎች አሸንፎ ለመሻገር ያስቻሉ ማህበራዊ ስሪቶቻችን ናቸው።

እነዚህን ማህበራዊ ስሪቶቻችንን ለማፍረስ በተለያዩ ዘመናት ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ሆኑ የነሱ ባንዳ ሆነው የተሰለፉ የውስጥ ሀይሎች ብዙ ጥረዋል። የህዝባችንን መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች የሚያሳድፉ ተግባራትን በተጠና መንገድ አቅደው ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱባቸው መንገዶች እሴቶች በፈጠሩት ጽናት ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

በተለይም ከፍጥረቱ ጀምሮ የህዝባችንን መንፈሳዊ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች ባፈነገጠ መልኩ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው አሸባሪው ሕወሓት እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ አገረ መንግስቱን ለማፍረስ እስከ ሲኦል ጥግ የመሄድ የከፋ እርግማንን የተሸከመ መሆኑ እውነታውን አሳሳቢ አድርጎታል።

ለዚህም ሲል በስልጣን ላይ በነበረባቸው 27 አመታት ለአገረ መንግስቱ መሰረት የሆኑ እሴቶች በተለያየ መንገድ ከመሸርሸር ባለፈ እሴቶቹ የነበራቸውን ማህበራዊ መሰረት ለማናጋት የተጓዘባቸው የሴራ መንገዶች እንደአገር ዛሬ ላይ ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈሉን ይገኛሉ።

ለእኩይ ተግባሩ ሲል የተለያዩ የጥፋት ትርክቶችን በመፍጠር ህዝባችን በትውልዶች መካከል ያካበታቸውን እና መገለጫው የሆኑትን ሰብዓዊነት፣ ወንድማማችነት፣ አብሮነት፣ ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር እሴቶችን አደጋ ውስጥ ከቷል። በህዝባችን መካከል አለመተማመንንና ጥርጣሬን ፈጥሯል።

ቡድኑ አገረ መንግስቱን አፍርሶ የራሱን አገረ መንግስት ለመፍጠር የሄደበት ስንኩል አስተሳሰብ፤ ገና ከውልደቱ ጀምሮ ለአገረ መንግስቱ ህልውና ከፍ ያለ ስጋት እንዲሆን አድርጎታል። ከስልጣን በህዝባዊ አመጽ ከተወገደ ማግስት ጀምሮ የቡድኑ ስጋትነት ወደሚጨበጥ አደጋ ተለውጦ ታይቷል። ለተጀመረው አገራዊ ለውጥ ዋንኛው ተግዳሮት ሆኗል።

በተለይም ቡድኑ በስልጣን ዘመኑ በህግና በመንግስት መዋቅር በመታገዝ ጭምር የዘራቸው የጥፋት ዘሮች የማህበረሰባችንን መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች በማቆሸሽ አዲሱ ትውልድ እንደ ትውልድ በአገረ መንግስት ግንባታ ውስጥ የሚጠበቅበትን ሀላፊነት እንዳይወጣ እያደረገው ይገኛል።

ይህን አገራዊ ተግዳሮት አሸንፎ ለመውጣት የሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ከሁሉም በላይ በቡድኑ የቆሸሹ ማህበራዊ እሴቶቻችንን የማጽዳት እና አጥርቶ ዳግም የማጽናት ስራን እንደሚጠይቅ ይታመናል። ለዚህ ደግሞ የሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ተቋማት ሀላፊነት ከፍ ያለ ነው።

እነዚህ ተቋማት የተጣለባቸውን ሀላፊነት በአግባቡ በመወጣት ትውልዱን በተሻለ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶች መገንባት ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ማድረግ ከሁሉም በላይ የሞራል ግዴታ አለባቸው። አገረ መንግስቱ በጠንካራ መሰረት ላይ የሚዋቀረው በታጠቀ ሰራዊት ብቻ ሳይሆን ከፍ ባለ የሞራል እሴት በተገነባ ትውልድ መሆኑን በአግባቡ ሊያጤኑት ይገባል።

የጀመርነው እና ህዝባችን ከፍ ባለ ተስፋ የሚጠብቀው የለውጥ ጉዞ ያለ ብዙ መንገጫገጭና ያለተጨማሪ ዋጋ ስኬታማ መሆን የሚችለውም ከፍ ባለ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶች የተገነባ ትውልድ መፍጠር ስንችል ብቻ ነው ። ይህንን ማድረግ ከቻልን እያሸነፍን እንሻገራለን ፤ እየተሻገርንም እናሸንፋለን!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የሽብር ቡድኖች የሐሰት ማደናገሪያ እንዳያዘናጋን

**በየኔነው ስሻው**

ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል እንዲሉ፤ ሐሰትን በመደጋገም እና ሕብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽም እንዲራባም በማድረግ ኑሯቸውንና ሕልውናቸውን የገነቡ የአሸባሪው ሕወሓትና ግብራበሮቹ ከመቼውም በበለጠ አዲስ ስልትና ጥምረት ፈጥረው እንደ አዲስ መንቀሳቀስ ጀምረዋል። ይህ ሐሰትን የመደጋገምና ለእውነት የቀረበ አድርጎ ለማስረጽ የሚሞከር የተቀባ ሃሳብና የፈጠራ ወሬ ታዲያ፤ በወጉ ታይቶ እንዲገራ ካልተደረገ ውሎ ሲያድር በሕዝቡ ውስጥ ውዥንብር መፍጠሩ፤ በዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም ዘንድ በድግግሞሹ ልክ ትኩረት መሳቡ አይቀሬ ነው።

ዛሬ ላይ አሸባሪው ሕወሓትና በውጭም፣ በውስጥም ያሉ መሰሎቹና ግብራበሮቹ ከእለት እለት እየተዳከመ የመጣውን ኃይላቸውን ለመጠገን፤ የሻከረ ግንኙነታቸውን ለማደስ፤ የተከዳ የጥፋት ጉዟቸውን የለዘበ በማስመሰል ወዳጅ ለማብዛት እንዲያስችላቸው የያዙት ይሄ የሃሰት መረጃና ፕሮፖጋንዳን በስፋት የማራገብ አካሄድ ነው። ይሄን ሲያደርጉ የጥፋት ዓላማቸውን ለማሳካት ያግዙኛል ያላቸውን ሁለት መንገዶችን በመያዝ ነው። አንደኛው በኢትዮጵያውያን መካከል ያልተገባ ጥርጣሬን በመፍጠር አንድነታቸውን ማላላት የሚያስችሉና የተጠኑ የፈጠራ ወሬዎችን ማባዛት ነው። ሁለተኛው፣ የዓለም አቀፉም ማህበረሰብ ትኩረት ይስቡልኛል ያሏቸውን የሰብዓዊና ሌሎች ጉዳዮች በራሳቸው መንገድ በሚያቀነባብሩት ሴራ አማካኝነት ከፍ አድርጎ ማስጮህ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

በቅርቡም እነዚህን ሁለት ጉዳዮች በአንድ ላይ ሊያጣምርምኝ ይችላል፤ በተለይም የውጭውን ማህበረሰብ ትኩረት አገኝበታለሁ፤ ግንኙነቴንም አድስበታለሁ፤ እግረ መንገድም በውስጥ ለምሰራው ፕሮፖጋንዳና የጥፋት ዘመቻ የተሻለ ነገር ያስገኝልኛል ያለውን በ “ምርኮኛ” ስም በሺዎች የሚቆጠሩ ሲቪሎችን፣ የታገቱ የመከላከያ ሰራዊት ቤተሰቦችን፣ ሾፌሮችንና ሌሎችም የሕብረተሰብ ክፍሎች ለቅቄያለሁ የሚል አካሄድ ነው። ይሄንንም በቀይ መስቀል ኮሚቴ በኩል ያከናወነው መሆኑን የተናገረ ቢሆንም፤ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ስለሚባለው ጉዳይ አላውቅም ማለቱ ግን የሕወሓትን የሽብር የቡድን የኖረና ያለ ውሸት ያጋለጠ ሆኗል።

ከሰሞኑ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት “በሃሰተኛ መረጃና ፕሮፖጋንዳ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ትኩረት ለመሳብ የሚደረግ ጥረት ቦታ የለውም!” ሲል ባወጣው መረጃ ይሄንኑ እውነት አረጋግጧል። በመግለጫው እንደተመላከተው፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ትክክለኛ ማንነቱን የዓለም ህዝብ እየተመለከተው መምጣቱንና በሃሰት ፕሮፖጋንዳ አሰልፎት የነበረው ድጋፍም መቀዛቀዙን ተከትሎ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ልብ እገዛበታለሁ ያለውን የ“ምርኮኞችን” ለቀቅሁ በማለት አጀንዳ ለማድረግ እየሞከረ ነው።

የወራሪነት፤ የአጥፊነትና የአገር አፍራሽ ትክክለኛ ገጽታውን ለመሸፈንና ሰላም ፈላጊ መስሎ ለመቅረብ የሚያደርገው መፍጨርጨር አንዱ መገለጫ ይህ ምርኮኞችን ለቀቅኩ የሚለው የሃሰት ትርክቱ ነው። የሽብር ቡድኑ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር ከዚህም በፊት የሃሰት መረጃዎችን በማቀነባበርና ተባባሪ ሃይሎችን እያሰለፈ የሴራው አካል ሲያደረግ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

የሕወሓት የሽብር ቡድን የአማራና አፋር አካባቢዎችን በሃይል ወረራ ስር አድርጎ በቆየባቸው ወቅቶች በግዳጅ ይዞ ኢሰብዓዊ ተግባራትን ሲፈጽምባቸው የነበሩ ሰዎችንና ለራሱ ፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ለማዋል ምርኮኛ በማለት የአገር ውስጥም ሆነ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማጭበርበር እየሞከረ ነው።

መንግስት ጉዳዩን አስመልክቶ እያደረገ ባለው ማጣራት በሽብር ቡድኑ ምርኮኞች ናቸው ተብለው የተለቀቁት አብዛኞቹ ዜጎች የመከላከያ ሰራዊት ከትግራይ ክልል ለቆ በወጣበት ወቅት በሽብር ቡድኑ ታግተው የቀሩ የሰራዊቱ ቤተሰብ አባላት መሆናቸው ታውቋል። በሌላ በኩል ከልዩ ልዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ለስራ ትግራይ ክልል ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሲቪል ነዋሪዎችን አግቶ የቆየው የሽብር ቡድኑ፤ አሁን የፖለቲካ ትርፍ አገኝበታለሁ ባለው የፕሮፖጋንዳ ድራማ የመከላከያንና የተለያዩ ጸጥታ ሃይሎችን መለዮ በማልበስ በምርኮኛ ስም አሰልፏቸዋል።

የሕወሓት ሽብር ቡድን ከሰሞኑ የጦርነት ከተት እያወጀና በይፋም እየተዘጋጀ መሆኑን ማስታወቁን ተከትሎ ያለችውን እንጥፍጣፊ ስንቅ ወደ ጦርነት ለማዞርና ለዳግም ጥፋት ራሱን እያዘጋጀ ለመሆኑ የአሁኑ ድርጊቱ ሁነኛ ማሳያ ነው። የዚህ እኩይ ሽብር ቡድን ተባባሪ የሆኑና በተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ እንደ ሸኔና ሌሎችም ታጣቂ ጽንፈኛ ቡድኖች የዚህ ፕሮፖጋንዳ ተባባሪዎች ናቸው።

ጉዳዩን አስመልክቶም የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን በመግለጫው እንዳለው፤ የሕወሓት የሽብር ቡድን ከእነዚህ ጽንፈኛ ቡድኖች አባላትን በመመልመልና በማሰባሰብ ከሸኔ የሽብር ቡድን ጋር በጋራ ሲያሰለጥናቸው የነበሩ ሰርጎ ገብ ሃይሎችንም በምርኮኛ ስም አደራጅቶ የእኩይ ተልእኮው ማስፈጸሚያና መረጃ መቀበያ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን በመንግስት በኩል የተደረገው ማጣራት አመልክቷል። በመሆኑም መላው ህዝብም ከዚህ ቀደም በሽብር ቡድኑ የሚነዙትን ሃሰተኛ ወሬዎች አላማና የሕወሓትን የአጥፊነት ተልዕኮ በማስታወስ አሁንም የሚያሰራጫቸው ወሬዎች የጥፋት ተልእኮውን ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸው መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል።

ከመንግስት ኮሙዩኒኬሽን መግለጫም ሆነ ከሕወሓት የሽብር ቡድን እና መሰሎቹ አሁናዊ እንቅስቃሴ መረዳት የሚቻለው፤ ቡድኑ አሁን ላይ ከፋኛ እየተገፋና በሕዝቡ ውስጥም በሚፈጽማቸው አፈናና በሚፈጥራቸው የከፉ ሰብዓዊ ቀውሶች ምክንያት ቅቡልነቱ እየከሰመ፤ በውስጥም በውጭም ጫና እየበረታበት በመጣ ጊዜ፤ ሌላ የማደናገሪያና ትኩረት መሳቢያ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ዘመቻዎችን መፍጠር ላይ መጠመዱን ነው። ይህ ደግሞ የቡድኑ የኖረ ባሕሪ፤ ዛሬም በዛው መንገድ ተጉዞ ሕዝቦችን ለመከፋፈልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ በማግኘት በኢትዮጵያ ላይ ዳግም ጫና እንዲያሳድሩ ለማድረግ የወጠነው ሴራ ነው።

ምንም እንኳን ይሄን መሰል አካሄዱ የኖረና የተለመደ ቢሆንም፤ በወጉ ተገንዝቦ ትክክለኛውን መረጃ ማውጣትና ለሕዝቡም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ማስረዳት ካልተቻለ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀርም። በተለይ ሕዝቡ በዚህ ተደጋግሞ የሚነገርና የሚራባ ሃሰተኛ ወሬና ፕሮፖጋንዳ እንዳይደናገር ተገቢውን መረጃ መስጠት፤ ሃሰቱን በእውነት አስደግፎ ማጋለጥና ማስረዳት ተገቢ ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ ሕዝብ በራሱም ከመደናገር ይወጣል፤ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብም የማስረዳትና የማሳወቅ ሚናውን በመወጣት ከሚፈጠረው ጫና፤ ከሚመጣው አደጋ ራሱንም አገሩንም መታደግ የሚችልበትን አቅም ይፈጥራል። ይህ እንዲሆን ደግሞ በሽብር ቡድኖች የሃሰት ፕሮፖጋንዳዎች ከመደናገር ወጥተን በእውነት ላይ የተመሰረተ መረጃን መቀባበል፤ በአንድ ቆመንም መታገል የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# «ከሚመረተው ውሃ 25 ከመቶ ይባክናል»

**አቶ ሞገስ አርጋው**
**የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ**

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ያገኘነው መረጃ እንደሚያስረዳው፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የቧንቧ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑት በ1893 ዓ.ም ነበር። ይህም የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነ ሰባት ዓመታት ቆይቶ ነው። የቧንቧ ውሃ አገልግሎት መጀመርን ተከትሎ አገልግሎቱን ማን ይስጠው የሚለውን መልስ መሻትም ግድ ነበር። በመጀመሪያ የሥራ ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መስሪያ ቤት ይህን ኃላፊነት ሲወጣ ቆየ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ በ1934 ዓ.ም የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት እንደገና ሲዋቀር ደግሞ «የውሃ ማደራጃ ዋና መስሪያ ቤት» በሚል ስያሜ እንደ አንድ የሥራ ክፍል የውሃ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ተቋቋመ።

የገፈርሣ ግድብና ማጣሪያ ጣቢያ፣ የለገዳዲ ግድብና ማጣሪያ ጣቢያ እንዲሁም የድሬ ግድብ ከፍተኛ ውሃ የማምረት አቅም ያላቸው የውሃ ምንጮች ናቸው። በተጨማሪም ጉድጓዶችና ሌሎች የከርሠ ምድር ምንጮች ከፍተኛ የሆነ ውሃ የማምረት አቅም ያላቸው ሲሆን የአዲስ አበባን ውሃ ጥም በመቁረጥ ባለውለታዎች ናቸው።

እነዚህ የታሪክ ሂደቶች ታልፈው፤ በሂደት የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 68/1963 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ፤ በድጋሚ በአዋጅ ቁጥር 10/87 በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ተቋቋመ። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 10/87 በተሰጠው ስልጣን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የውሃ መገኛዎችን በመጠቀም እና የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓትን በመዘርጋት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ከአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን ዕድገት ጋር የሚመጣጠን የንፁህ ውሃ አቅርቦት እና የዘመናዊ ፍሳሽ ማስወገጃ አገልግሎት ለከተማዋ ነዋሪ በበቂና በአስተማማኝ ሁኔታ ተደራሽ ለማድረግ በርከት ያሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በማዋቀር ለህብረተሰቡ አስፈላጊውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በዛሬው ዕትማችንም የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የውሃ ደንበኞች ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሞገስ አርጋው የተቋሙን አሠራር አስመልክቶ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ያደረጉትን ቆይታ ይዘን ቀርበናል።



ፎቶ፦ ገባቦ ገብሬ

**አዲስ አበባን በ12 ቅርንጫፍ ለመምራት ጥናት ተጠናቋል። እስከ 2010 የነበረው ከ42 የመሰብሰቢያ ማዕከላት በአሁኑ ወቅት ወደ 350 አድጓል**

**አዲስ ዘመን፡- ባለስልጣኑ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ደንበኞች አሉት?**

**አቶ ሞገስ፡-** ደንበኞቻችንን የውሃ እና ፍሳሽ ብሎ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። በአሁኑ ወቅት ከውሃ አኳያ ወይንም ውሃ ቆጣሪ በቤታቸው የተገጠመላቸው 600ሺ ደንበኞች አሉ። ከፍሳሽ አኳያ ወይንም በዘመናዊ መንገድ መስመር ተዘርግቶ ፍሳሽ የሚያስወግዱ ደንበኞች ደግሞ 198ሺ በላይ የሚሆኑ ናቸው። ይህ ቁጥር በየጊዜው አዳዲስ ደንበኞች እየመጡ ሲሄድ ቁጥሩ እየጨመረ የሚሄድ ነው። አሁን ባለስልጣኑ የሚያውቀው ቁጥር ግን ከላይ የገለፅኩት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የባለስልጣኑን አገልግሎት ለማግኘት የሚሹ ደንበኞች ፍላጎትና ዕድገት ምን ይመስላል?**

**አቶ ሞገስ፡-** የደንበኞችን ፍላጎት በሁለቱም መንገድ ነጣጥሎ ማየት ይገባል። ከውሃ ቆጣሪ ፍላጎት አኳያ ራሱን የቻለ ታሪክ አለው። የዘመናዊ ፍሳሽ መስመር መጠቀምም ራሱ የተለየ ባህሪ አለው። ንፁህ ውሃ ለማግኘት ከሚጠይቁት ከመሃል ከተማ ነዋሪዎች አኳያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ነው። ይህም በየጊዜው ጠይቀው ምላሽ ያገኙ ናቸው። በሌላ ጎኑ በጋራ መኖሪያ ቤቶችና ማስፋፊያ አካባቢዎች ከፍተኛ ፍላጎት አለ። በመሆኑም በመሃል ከተማ እና በማስፋፊያ አካባቢ ያለው በድምር ሲታይ ግን የደንበኞች ፍላጎት እየጨመረ ነው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ በየዓመቱ ከ10ሺ እስከ 15ሺ የውሃ ቆጣሪዎች ይቀጠላሉ። የሪል ስቴቶችም የዚሁ ተጠቃሚ ናቸው። ባለስልጣኑ 1962 ዓ.ም ሲቋቋም ፍሳሽ ቆጣሪ ቅጥያ ዕድገት በጣም አዝጋሚ ነው። ፍሳሽ አገልግሎት በስፋት ሲሰጥ የነበረውና አሁንም ድረስ ፍሳሽ ማንሻ በተሽከርካሪዎች ነው። በዚህም ደንበኞቻችን ሁለት ዓይነት ባህሪ አላቸው። አንደኛው በተሽከርካሪ አገልግሎት የሚያገኙ ሲሆን ሁለተኛው ግን ከቤታቸው ቀጥታ የፍሳሽ መስመር የሚዘረጋላቸውና ከመስመሩ ጋር የሚገናኙ ናቸው። በአፍሪካ ቀዳሚ ከሆኑት የፍሳሽ ማጠራቀሚያዎች አንዱ የሆነው የቃሊቲ ፍሳሽ ማጠራቀሚያም ለዚህ ሥራ መሳካት ትልቅ ጥቅም አለው። ሁለቱንም ስንመለከት ፍሳሽ በመስመር መጠቀሙ ፍላጎት እያደገ ነው። ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በመሥራታችን እየተሻሻለ ነው። ሌላው ትልልቅ ህንፃዎች እና መሃል ከተማ ያለው በተሽከርካሪ ብቻ ተደራሽ መሆን አስቸጋሪ ስለሚሆን ወደዚህ እየገቡ ነው። በዚህም ባለፉት ሦስት ዓመት ከ60ሺ ወደ 198ሺ አድጓል። እየቀነሰ የመጣው በተሽከርካሪ ፍሳሽ ይነሳልን የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ከመኖሪያ ቤት ውጭ የመክፈል አቅማቸው የተሻሉ የምንላቸውን ደንበኞች ለሦስተኛ አካላት አሳልፈን (out sorce) አድርገናል። ሌላው የቀነሰበት ምክንያት ዘመናዊ ፍሳሽ ማስወገጃ በበራቸው ላይ የሚያልፍ ነዋሪዎች በአስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ከዋና መስመር ጋር እያገናኙ ነው። በዚህም በሂደት የዘመናዊ መስመር እየተጠቀሙ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በፍሳሽ አወጋገድ ከደንበኞችና ከተማዋ ነዋሪዎች ፍላጎት አኳያ የባለስልጣኑ ምላሽ አሰጣጥና አፈፃፀም እንዴት ይለካል?**

**አቶ ሞገስ፡-** የፍሳሽ ሥራችን ለዘመናት የተረሳ ጉዳይ ነበር። የመጀመሪያው ነገር ተቋሙ ከተመሠረተ ጀምሮ ሲሰራበት የነበረው ውሃ ምርትና ስርጭት ላይ ያተኮረ ነበር። በወቅቱ ለዚህም በቂ ምክንያት ነበር። የከተማው በጀት ለመንገድ፣ መብራት፣ ለውሃ ስርጭት የተወሰነ ስለነበር በወቅቱ ፍሳሽ ማንሳት ሥራውና ዘመናዊ ፍሳሽ አወጋገድ ላይ ብዙ ትኩረት አልተሰጠም ነበር። ሽፋኑም እስከ 2010 ዓ.ም 15 እስከ 19 ከመቶ ብቻ ነበር። በእርግጥ በቀላሉ በመንግስት በጀት ብቻም የሚመለስ አይደለም። ይህ የሚያሳየው ለበርካታ ዓመታት የተዘነጋ ነበር።

የፍሳሽ መሰረት ልማት ከውሃ መሰረተ ልማት ያልተናነሰ እንዲያውም በበለጠ መልኩ በጀት የሚፈልግና በቴክኒኩም ብዙ ነገር የሚጠይቅ ነው። ይሁንና ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የከተማው ዕድገት ከትንንሽ ቤቶች ተነስቶ በጣም ግዙፍ ህንፃዎች እየተበራከቱ ነው። እነዚህንም በተሽከርካሪ የፍሳሽ አወጋገድ ማስተናገድ አይቻልም። ለአብነት ሲግናል አካባቢ ለሚገኙ መኖሪያዎች በቋሚነት መኪና ተመድቦ ነበር ፍሳሽ የሚያስወግደው። ከተማዋ ንፁህ ለምን አልሆነም የሚል ጥያቄ በብዛት ይነሳል። ግን ዘመናዊ ቆሻሻ አወጋገድ ከሌለ ለጥያቄው መልስ ማግኘት አይቻልም። ለዚህ ምላሽ ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀትና ዘመናዊ ፍሳሽ መስመር በመገንባት የሚመለስ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በተሠራው ሥራ ሽፋኑ ወደ 30 ከመቶ የደረሰ ሲሆን በተያዘው በጀት ዓመት ደግሞ 32 ከመቶ የማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

ይህ ሲሠራ ብዙ ፈተና ነበር። ህብረተሰቡ ዘመናዊ ፍሳሽ አወጋገድን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ ነው። ሕብረተሰቡ ይህን ለመጠቀም አሁንም ፈተና ነው። ግን ወደ አሰራር ለመግባት ባለስልጣኑ በርካታ አመቺ መንገዶችን እየተከተለ ነው። ሁለተኛው ፈተና የከተማው ልማት ፊትና ኋላ በመሆኑ መናበብ አልተቻለም። አንዳንዶቹ ቀድመው ሲሄዱ ሌሎች እንደ አዲስ አሁን እየጀመሩ ነው። ከተማዋ ከልማት አንፃር በፕላን ላይ ተንተርሳ ከጅምሩ ባለመሠራቱ ፈተናዎች በርክተዋል። በዚህም የተነሳ ወሰን ማስከበር ስራው እስካሁንም ከፍተኛ ፈተና ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- የወሰን ማስከበር ስራውና አንዱ ሌላው የሚወቅስበት ጊዜ መቼ ያበቃል?**


**አቶ ሞገስ፡-** መጀመሪያ መታወቅ ያለበት የተቋማትን ስልጣንና ተግባር ነው። መገናኛ ብዙሃንም ሆኑ ህብረተሰቡ ሊረዱት የሚገባው እያንዳንዱ ተቋም ተልዕኮ ምን እንደሆነ ነው። ይህን በሚገባ ባለመለየት አንዱ ባጠፋው ሌላው ይወቀሳል። ለአብነት መብራት፣ ውሃና ቴሌ ሥራቸው መሬት ላይ ነው የሚከናወነው። ከእነዚህ ጋር በጋራ መስራት የሚያስችለን መንገድ አለ።

# ተጠየቅ

በተለይም አዳዲስ ሰፈሮችና ማስፋፊያ አካባቢዎች በመነጋገርና በመመካከር መስራት ይቻላል። ነገር ግን ሌሎች መሰረተ ልማቶች ቀድመው በሰሩበት ቦታ እኛ እንደ አዲስ ስንገባ ያልተናበበ ሥራ ሊኖር ይችላል። አሁንም አንዱ ተቋም ከሌላው ቀድሞ ቢገባ በቢ.ፒ.አር የተቀመጠ አሰራር ስላለ መናበብ ይቻላል።

ሌላው መናበቡን አስቸጋሪ የሚያደርገው የአገሪቱ አቅም ሲሆን፤ ፕላንና ህጋዊ የሰነድ ማረጋገጫ ከሌላቸው ስራው አስቸጋሪ ይሆናል። የአገሪቱ አቅም ውስን መሆን ፈተና ነው። በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ የተዘረጉ መስመሮች አሁንም አገልግሎት እየሰጡ ነው። ይህን መቀየር ይገባል። ለዚህ ታዲያ በመንግስት በጀት ብቻ የሚከናወን ሳይሆን ሌሎች አጋዥ አካላትም ድጋፍ ይፈልጋል። ሌላው ባለስልጣኑ ውሃ ለማስገባት ጉድጓድ ተቆፍሮ የሚቀመጥ ከሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆነን እየፈታን ነው።

ብዙ ችግሮችን በመነጋገር እየፈታን ነው። ነገር ግን አልፎ አልፎ የተወሰኑ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል። ይሁንና ህብረተሰቡ የሚያነሳቸው እውነተኛ ጥያቄዎች የሉም ወይ ከሆነ መልሱ አለ ነው። እነዚህን በሂደት የምንፈታው ነው። የሆነው ሆኖ በማንኛውም አካል ችግር ቢኖርም ወይም ቢፈጥርም እንደ ከተማ አስተዳደር ስለሆነ ለመፍትሄውም በጋራ እየሰራን ነው። ይህን የሚያቀናጅ አካል አለ። ከዚህ በዘለለ ከነዋሪዎች ጋር ፎረም ስላለን ችግራችንን በቀላሉ ለመፍታት እያስቻለን ነው። ጠቅለል ሲደረግ ግን ከዓመታት በፊት የነበሩ እሰጣ ገባዎች በአሁኑ ወቅት በብዙ እጥፍ እየቀነሱ ነው። ውሃና ፍሳሽ፣ ቤቶች እና መብራት አንዱ ከሌላኛው በጣም የተሳሰሩ ስለሆኑ ተናበን ለመሥራት እንገደዳለን።




**አዲስ ዘመን፡- የደንበኞችን ፍላጎት ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ታካሂዳላችሁ፤ ደንበኞቻችሁ እናንተን እንዴት ይገልጿችኋል?**

**አቶ ሞገስ፡-** ደንበኞችን ነባራዊ ፍላጎት ስንመለከት፤ አንደኛው እንደነዋሪ 24 ሰዓት ውሃ የማግኘት ፍላጎት አለ። ሌላኛው በአሁኑ ወቅት ውሃ በከተማዋ ውስጥ በብዛት በሬሽን መሆኑ ይታወቃል። በሣምንት ሦስት ቀን የሚያገኙ ከሆነ በሣምንት አራት ቀን የማግኘት ፍላጎት አለ። ሳምንቱን ሙሉ ውሃ የሚያገኙ ካሉም ምንም ሳይነካ ከሳምንት ሳምንት ማግኘት የሚፈልጉ አሉ። እነዚህን ፍላጎቶች በደንብ እናውቃለን፤ ጥናትም ሳይደረግ ይታወቃል። ነገር ግን ህብረተሰቡ የሚፈልገው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ማግኘት ይፈልጋል። እኛም ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲያገኝ እንፈልጋለን። አሁን የሚመረተው እና የሚሰራጨው ውሃ መጠን ይታወቃል። በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል አለመመጣጠን አለ።

በመብራት መቆራረጥ ከሚመረተው ውሃ እስከ 25 ከመቶ ይባክናል። የውሃ ጉዳይ ቀላል አይደለም። ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች አሉት። የሆነው ሆኖ ግን የተመረተው ውሃ ህብረተሰቡ ዘንድ ፍትሃዊ ሆኖ መድረሱ ነው። እኛ እዚህ የሚገጥመን ፈተና ውሃ ከተመረተ በኋላ የራሱ ሂደቶች አሉ። አንዳንዱ በግራቪቲ ሲሄድ፤ ሌላው በፓምፕ ይሄዳል። በዚህ ወቅት መብራት ከተቆራረጠ የተለመደው ፈረቃ ይዛባል። ይህ አንዱ የመልካም አስተዳደር እጦት ምንጭ ነው፤ ደግሞ ትክክል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በባለስልጣኑ እይታ በሬሽን የሚሰራጨው ውሃ አሰራሩ ፍትሐዊ ነው?**

**አቶ ሞገስ፡-** ፍትሐዊነቱ መቶ በመቶ የተረጋገጠ ነው አንልም። ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች አሉ። መብራት ይጠፋል፤ አንዳንዴ ደግሞ መስመር ይሰበራል። አልፎ አልፎ ሥራችን በሦስተኛ ወገን ስለሚሠራም ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ይህን ህብረተሰቡ ይገነዘባል። እኛ በውሃ መስመር ዝርጋታና ቁፋሮ፣ በፍሳሽ መስመር ዝርጋታ እስከ 10ሺ ለሚሆኑ ወጣቶች ሥራ ፈጥረናል። አሰራራችን በሰው ሃይል የሚሰራ ስለሆነ ክፍተቶች አሉ። በዋናነት ግን የተመረተው ውሃ ወደየትም አይሄድም።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ አካባቢዎች ውሃ ያለመቆራረጥ ሲያገኙ የሌሎች ደግሞ ጥያቄ በሚያስነሳ መንገድ የሚቆራረጠው ለምንድን ነው?**

**አቶ ሞገስ፡-** በሁለት መንገድ ማየት ጥሩ ነው። 24 ሰዓት ውሃ የሚያገኙ ስድስት ወረዳዎች አሉ። ከዚህ ውጭ በፈረቃ ነው። ሌላው በአንድ አካባቢ ከመንገድ ቀኝ እና ግራ ሆነው አንዱ ውሃ ሲያገኝ ሌላው አያገኝም። ይህ የሆነው ከተማችን የውሃ መገኛ በተለያየ ቦታ እና መንገድ ነው። የሚመራውም በሰው ነው። አንዳንዴ ህብረተሰቡ ውሃ እንዲያገኝ ብለን ብዙ አሰራር እንከተላለን። ቴክኒካል ነገሮችን አስተካክለን ነው ውሃ የምናሰራጨው። ሌላው ቀርቶ በአንድ መስመር ላይ ሆነው አንዱ ደንበኛ ውሃ ሲያገኝ ሌላው ደንበኛ ውሃ ላያገኝ ይችላል። ይህ የሚሆነው «ጌትቫልቭ» ሲዘጋ እንኳን ካለማየት ሊመነጭ ይችላል። ሌላው የቆየ የብረት መስመር እየዛገ ሲመጣ ውሃ መስመሩን ይዘጋል። ይህን ችግር ለማቃለል ደንበኞቻችን ውሃ መስመሩን እንዲቀይሩ እንመክራለን። ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ሰራተኞቻችን ችግር ሊኖርባቸው እንደሚችል ይታመናል። ከተማችን ውስጥ የውሃውን ስርጭት ፍትሃዊ ለማድረግ የተገጠሙ 112 በላይ ቫልቮች አሉ። አልፎ አልፎ ስርቆት ያጋጥመናል ይህም የውሃ ስርጭቱ ላይ እክል ይፈጥራል። ይህን ለማረም ህብረተሰቡ መተባበር አለበት። ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶችን በብዛት በመክፈት ለደንበኞች ጥያቄ ለመመለስ እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እውነት ደንበኞችን ከመጉሳላት ለመታደግ አዳዲስ አሰራር ተዘርግቷል?**

**አቶ ሞገስ፡-** አዎ! ለምሳሌ ቅርንጫፎቻችሁ ተደራሽ አይደሉም የሚል ጥያቄ ነበር። በዚህም አራት ቅርንጫፍ ተጨምሮ አዲስ አበባን በ12 ቅርንጫፍ ለመምራት ጥናት ተጠናቋል። እስከ 2010 የነበረው ከ42 የመሰብሰቢያ ማዕከላት በአሁኑ ወቅት ወደ 350 አድጓል። አገልግሎት አሰጣጡም ኋላቀር ነው የሚል ወቀሳ ነበር። ለክፍያ ይሰለፉ የነበሩትን ጫና ለማቃለል በአንድ ዓመት አምስት የክፍያ አማራጮችን ጀምረናል። ዊንዶ ሰርቪስ፣ ኢንተርናል ባንኪንግ፣ ሲቢኢ ብር፣ ኢድማርክ አካውንት እና ሞባይል ባንኪንግን ወደ ሥራ አስገብተናል። ይህ ትልቅ ለውጥ ነው።

ሌላኛው የንባብ ጥራት ችግር አለ በሚል ሕብረተሰቡ ቅሬታ ነበረው። ይህን ሙሉ ለሙሉ ለማቃለል በቢቢነስ ፕላን ተካቶ አንድ አንባቢ ሲመጣ በአምስት ሜትር ርቀት ቆጣሪውን ማንበብ ይችላል። ይህ ተሰርቶ ግን ሙሉ ለሙሉ ከስህተት የፀዳ ነው የሚል መከራከሪያ የለም። ሆኖም በቀጣይ ችግሮችን በስፋት ለማቃለል ስትራቴጂካሊ ለማቃለል እንሠራለን።

የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድም ላይ ቀደም ሲል ከ30 ሜትር ርቀት በላይ ከሆነ ማስተናገድ አስቸጋሪ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ይህን ችግር ለማቃለል እስከ 150 ሜትር ርቀት አገልግሎት የሚሰጡ 90 ተሽከርካሪዎች እስከ ሐምሌ ድረስ ወደ አገር ውስጥ ይገባሉ። በአጠቃላይ ባለስልጣኑ በአጭርና ረጅም ጊዜ ውስጥ የሕብረተሰቡን ጥያቄዎች ለመመለስ እየሠራ ሲሆን ከተማ አስተዳደሩም አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቷል። በርካታ ሥራዎቻችንም «አውት ሶርስ» አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ የመጠጥ ውሃ ለጓሮ አትክልትና ለመኪና እጥበት እየዋለ ነው። መጠጥ ውሃ በፈረቃ በሆነበት ከተማ ይህ አግባብ ነው?**

**አቶ ሞገስ፡-** በከተማው የውሃ አቅርቦትና ፍላጎት የተጣጣመ አይደለም። ይህን የሚያባብሱ ሁኔታዎች አሉ። አንደኛው ህገ ወጥ የውሃ አጠቃቀም ነው። ሌላው ትልልቅ ሮቶ መሬት ውስጥ በመቅበር ውሀ መጥለፍ «ሃይጃክ» ያደርጋሉ። ይህ በፈረቃ ውሃ ማግኘት ያለባቸው ነዋሪዎች ውሃ ሳያገኙ ይቀራሉ። መጠጥ ውሃን ከመጠጥ ውጭ ለሌላ አገልግሎት መጠቀም ይስተዋላል።

ትልቁ ችግር መንግስታዊ ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ንፁህ የመጠጥ ውሃን ለግንባታ አገልግሎት ይጠቀማሉ። አቅም ያላቸው ትልልቅ ሆቴሎች ግቢያቸውን ለማስዋብና ለዕፀዋት ንፁህ ውሃ ይጠቀማሉ። እኛ ከ2010 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ የመጠጥ ውሃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ህግ አውጥተናል። ግን ህንፃ የሚገነባ ሰው ምን ያድርግ ለሚለው ምላሽ ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ አጣርተን የምናስወጣው በንጽህናው ከመጠጥ ውሃ ያልተናነሰ ውሃ ወደ ወንዞች እየተለቀቀ ነው። በመሆኑም ለመኪና እጥበትና ግንባታ አገልግሎት የሚውልበት ሁኔታ አመቻችተናል። ነገር ግን ከ2010 ዓ.ም በፊት ውሃ ቆጣሪ የገባላቸውና የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው መኪና አጣቢዎች ንፁህ ውሃውን እየተጠቀሙ ነው። ከዚያን በኋላ ግን ይህ አሰራር ቆሟል፤ አዳዲስ ጥያቄዎችም ዝግ ናቸው። እኛ አገር ውሃ በጣም ርካሽ ስለሆነ እንጂ እንደ ሌላው አገልግሎት ውድ ቢሆን የሥራ ዕድል ፈጠራ የሚለው አይታሰብም።

**አዲስ ዘመን፡- ሆቴሎችን ጨምሮ በርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የከርሰ ምድር ውሃ አውጥተው እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ተቀምጦ ነበር። ይህን በማይተገብሩት ላይ ዕርምጃ እየተወሰደ ነው?**

**አቶ ሞገስ፡-** ወደዚህ ያስገባን ችግሩ እንጂ እንደ አሰራር ማስገደድ አይቻልም። ከተማውን፣ መንግስትና ተቋሙን ከማገዝ አኳያ እንጂ በአሰራር ጉድጓድ እንዲቆፍር አንድ ሆቴል አይገደድም። ውሃ ከየትም አምጥቶ ማቅረብ ያለበት ባለስልጣኑ ነው። አንደኛው የባለስልጣኑ የገቢ ምንጭ ከውሃ ሽያጭ ስለሆነ ነው። ወጪና ገቢ አመጣጥኖ መምራት እንጂ ይህ ሥራዎችን በሙሉ ለሌላ አሳልፎ መስጠት አሠራር ሆኖ መቀጠል የለበትም። ውሃ እና ፍሳሽ ከአጠቃላይ ገቢው 80 ከመቶ የሚገኘው ከውሃ ሽያጭ ነው። ሌላው ይህን በፍርድ ቤት መክሰስ አንችልም። ሦስተኛው ጉዳይ ከጤና አኳያም ይህ አሰራር ብዙ ስለማይመከር ይህ አስገዳጅ መሆን አለበት የሚል አቋም የለም። ይህ አሰራር የከተማውን አሁናዊ ችግር ለማቃለል የሚያግዝ ነው። ይህ በሂደት የሚቆም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የባለስልጣኑ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የደንበኛና መንግስት ፍላጎት እንዲጣጣም ምን አይነት አሰራሮች ተቀይሰዋል?**

**አቶ ሞገስ፡-** የመጀመሪያው አገልግሎት አሰጣጥና የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የተቋሙን የማስፈፀም አቅም ማሳደግ ነው። ቴክኖሎጂ የዚህ አካል ነው። መሰረታዊው ነገር መዋቅራዊ አደረጃጀት ማስተካከል ይፈልጋል። 600ሺ በላይ ደንበኞችን ይዞ ውሃ አምርቶ፣ መስመር ዘርግቶ አሰራጭቶ እና ገቢ ሰብስቦ ደንበኛን አስደስታለሁ ማለት ከባድ ነው። በመሆኑም አሰራሮችን ማዘመን ይገባል በሚል አሰራር መዋቅራዊ ማስተካከያዎች ተደርገዋል።

ችግሮችን ለማስተካከል የውጭ አገራትን ተሞክሮ በመቅሰም ወደ ተግባር ተገብቷል። ቴክኖሎጂዎችን መተግበር ተጀምሯል። አይቻሉም የሚባሉ አጀንዳዎች ተዘግተው እንደሚቻል አሳይተናል። አሰራሮችን በየጊዜው እያዘመንን ነው። አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችም ተሻሽለዋል። ለምሳሌ አርሶ አደሮች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ውሃ አያገኙም ነበር። ይህን እና መሰል አሰራሮችን የህዝብን ፍላጎትና የመንግስትን አሰራር በማክበር እየሰራን ነው። ቴክኖሎጂ ተኮር አሰራሮች በብዛት እየተተገበሩ ነው። የፋይናንስ አሰራራችን አውቶሜትድ ሆኗል። አሰራራችን በሲስተም የተደገፈ ነው። የካዳስተር ሲስተማችን ከአንድ ዓመት በኋላ ይጠናቀቃል። በርካታ አሰራሮቻችን በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነን። ጥያቄዎችን ለመመለስ ተቋሙ ግልጽ ቢዝነስ ፕላን አለው።

**አዲስ ዘመን፡- የተቋሙ አንኳር ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሞገስ፡-** የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ግብዓቶች የሚገቡት ከውጭ አገር ነው። በዚህም ውጭ ምንዛሪ እጥረት አለ። ከዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸው ከ100ሺ በላይ ደንበኞች ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ለመክፈል ዝግጁ ያልሆኑ ናቸው። ሌላው ሥራ ትተን ቆጣሪ ለመቁረጥ እንሄዳለን። በዓመት እስከ 54ሺ ቆጣሪ ቆርጠናል። ይህ ትልቅ ፈተና ነው። ውሃ በጣም ርካሽ ታሪፍ ነው። አንድ ሜትር ኪዩብ ውሃ ለማምረት 30 ብር እናወጣለን፤ ለህዝብ የምናቀርበው ግን በ2 ብር ከ40 ሳንቲም ነው። ተቋሙ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች አሉ። ጥቂት ደንበኞች ምናልባትም ከ20 እስከ 25 በመቶ ደንበኞች በሚፈጥሩት ችግር ተቋሙ በፋይናንስ እጥረት እንዲፈተንም ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም በዚህ ላይ የመገናኛ ብዙሃን የጠራ መረጃ ይዘው እንዲያግዙን እንፈልጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ ሆነው ለባለስልጣኑ ያቀረብናቸውን ጥያቄዎች ምላሽ ስለሰጡ እናመሰግናለን።**

**አቶ ሞገስ፡-** እኔም የተቋማችንን አሰራር በተመለከተ ለህዝቡ መረጃ ስለምትሰጡ እናመሰግናለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## አሸጋግረን እንለፍ

ይህ ጸሐፊ ከማኅበራዊ ሚዲያ ቱማታ ይልቅ ስሜቱንና ሃሳቡን ሰብስቦ በመጻሕፍት ውስጥ ራሱን ቢሸሽግ ይመርጣል። የስሜትን ወጀብ ጸጥ አድርጎ በተረጋጋ መንፈስ እውቀትን ለመገብየት መጻሕፍት በእጅጉ ተመራጭ ናቸው። ዘመነ ቴክኖሎጂ ግን ሕዝበ አዳምን ከመጻሕፍት ለማፋታት አጠንክሮ በመስራት በልዩ ልዩ አዳዲስ ግኝቶች የማማለሉን ዘመቻ አጧጡፎ የተያያዘው ይመስላል።

ምንም እንኳን ዘመኑ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ "እንድንሰግድ" ጫናውና ጠቀሜታው ቀላል ባይሆንም ከመጻሕፍት ንባብ ጋር ፍቺ ፈጽመን እንኑር ማለቱ ግን አግባብም፣ አዋጭም፣ ተገቢም አይደለም። ሰሞኑን እያነበብኩት ብቻም ሳይሆን እያብላላሁት ጭምር ያለው "Die Empty" በሚል ርእስ Todd Henry የተባሉ ደራሲ የጻፉትን ድንቅና ተወዳጅ መጽሐፍ ነው። ምናልባትም በቅርብ ጊዜያት ካነበብኳቸው መጻሕፍት መካከል ይኼኛው በግንባር ቀደምትነት በአንቱታ ያከበርኩት መሆኑን ለአንባቢያን መመስከር እወዳለሁ። እንዲያነቡትም አደፋፍራለሁ።

የመጽሐፉን ርእስ ለዚህ ጽሑፌ ተውሼ ወደ ቋንቋችን ለመመለስ የሳምንታት ትግል ቢፈጅብኝም አልተሳካልኝም። ቃል በቃል በመተርጎም "ባዶ እንደሆንን እንሙት"፤ አይሉት ነገር ትርጉሙ ሌጣና መላ ቢስ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌላ ይዘት ጭምር ስለሚያጋድል የሚሞከር አልሆነም። "አውርሰን እንሙት" ለማለት ሞክሬም የቋንቋችን ዐውድ አልፈቅድ ቢለኝና ትርጉም አልባ ቢሆንብኝ እርግፍ አድርጌ ተውኩት። ለማንኛውም ከብዙ ሙከራዎች መካከል ምርጫው አሸንፎ ሳይሆን፤ ይሻላል ያልኩት ተዛማጅ ትርጉም ከላይ በርእስነት የተጠቀምኩበትን ሀረግ ነው - "አሸጋግረን እንለፍ" የሚለውን።

ደራሲው በመጽሐፋቸው ውስጥ ለማስተላለፍ የፈለጉት ዋነኛው ጭብጥ በአንድ ዐረፍተ ነገር ይቅረብ ከተባለ፤ "ነገ ማለፍህ ስለማይቀር፤ የተሰጠህን ችሎታ፣ ፀጋና መክሊት ለተከታዩ ትውልድና ለሀገርህ ሳታሸጋግር የሰነፍ ሰው ሞት እንዳትሞት ተጠንቀቅ" የሚል መልእክትን ነው። ይህንን አንኳር ሃሳብ በብዙ ምሳሌዎችና ማሳያዎች ለመዘርዘር የሞከሩት የተዋጣላቸው በርካታ አሳማኝ ትንታኔዎችን በመጠቀም ነው።

እኔም ከዚህ መጽሐፍ ያገኘሁትን እውቀት ለአንባቢዎቼ ለማጋራት ልቤ የተነሳሳው የአገራችን ወቅታዊና አሳሳቢ ሁኔታዎች በንባቤ መሃል ፍንትው ብለው እየታዩኝ ንባቤን እስከማሰናከል ድረስ ደርሰው እንደነበርም ሳልሸሽግ አላልፍም። ስለዚህም ሙሉውን የመጽሐፉን ሃሳብ ሳይሆን ቁራሹንም ቢሆን ማጋራቱ ይበጅ ስለመሰለኝ እነሆ የንባቤን ማዕድ እንድትጋሩልኝ ይድረስ ብያለሁ።

### እንቀጥል…

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ፤ "መጽሐፍ መክብብ" በሚል ርዕስ የሚታወቅ አንድ ድንቅ መጽሐፍ አለ። "የጥበብ ማዕድን" የሚባሉ እውቀቶችን አምቆ በመያዙ ተወዳጅና ተጠቃሽ ከሆነው ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥቂት ስንኞችን በመዋስ እንደ መደላድል ልጠቀምበት። እንዲህ ይነበባል፤ "ከመልካም ሽቱ ይልቅ መልካም ስም ይሻላል። ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ይልቅ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል፤ እርሱ የሰው ሁሉ ፍጻሜ ነውና፤ ሕያውም የሆነ በልቡ ያኖረዋልና" (ምዕራፍ 7፥1-2)።

የዚህ ጥቅስ መልእክት ባጭሩ "ሞት የሚባል አይቀሬ እዳ እንዳለ አስብ። የደስታህ ውሎ የሞትህን እውነታነት አይጋርደው። ተግባርህ የስምህ ሽቱ ሆኖ በሕያውነት እንዲጠቀስልህ ከፈለግህ ዛሬን በጎ በማድረግ አስተናግደው" የሚል ነው። ከሞት ጋር ሕይወት መታሰቡ፣ ከህልፈት ጋርም የመኖር ጉጉት መጎዳኘቱ የማይቀር እውነታ መሆኑ እንዳይዘነጋ በማስታወስ ጭምር። ከላይ በመንደርደሪያችን ላይ የተጠቀሰው የሚስተር ሄኒሪ መጽሐፍ በዋነኛነት የሚሞግተንም "ሞት በቀጠሮ የማይመጣ ከሆነ ስለምን ለአገርና ለትውልድ በጎ ከማድረግ እንዘናጋለን? ስለምንስ ለመተንበይ ካልሆነ በስተቀር ለመኖር ዋስትና በማይሆነን ነገ በሚሉት ተስፋ እየተታለልን እንሞኛለን። ለምንስ ጠቃሚና በጎ የሆነውን መክሊታችንን ታቅፈን እንቀበራለን" የሚል ግዙፍ ሃሳብን ነው።

ጸሐፊው፤ "ያንተ ቀን ዛሬ ነው። ዛሬ ማድረግ የሚገባህን ለነገ አታሳድር። ለነገ ማሳደር ብቻም ሳይሆን ንፍገትንም አትለማመድ። አንተ ራስህ የብዙዎች ውጤት መሆንህንም አትዘንጋ። በአእምሮህ የተከማቸው እውቀት፣ በእጅህ ላይ የተጠራቀመው መክሊት በብዙዎች ተሳትፎ የተገኘ እንጂ የአንተ ብቻ ጥሪት አይደለም። አንኳን ለነገ አሳድሬያለሁ እያልክ የምተመካበትን ሃብትና እውቀት ቀርቶ እየኖርክባት ያለችው ጀንበር ራሷ የአንተ አይደለችም። ጉዞዋን ጨርሳ በነገ ሌላ ጀንበር ትተካለች። ስለዚህም ነገ የምትለው የተስፋ ዕለት ምን ይዞ እንደሚመጣ ስለማታውቅ አትዘናጋ" እያለ በብርቱ ሃሳቦች ይሞግተናል።

ሙግቱ የሚያፈናፍን አይደለም። የጥበብ ተሰጥኦ ካለህ አቅምህን አሟጠህ በዛሬዋ ጀንበር ለሕዝብህ አስተላልፍ። ሃብት ካለህ ያለ ስስት ዛሬ የምትሞቃት ጸሐይ ሳትዳምን ለትውልድ የሚተላለፍ ፍሬ አፍራበት። የአንተ እውቀት በሚያስፈልግበት ቦታ ንፍገት አሸንፎህ በአእምሮህ ጓዳ ካዝና ውስጥ የተከማቸውን ጥብብ ቆልፈህበት ለነገ አታሸጋግረው። ነገ ያንተ ስለመሆኑ በምን እርግጠኛ ሆነህ ለለጋስነት ትዘገያለህ?" እያለም የራሳችን ከምንለው እምነት ጋር ያፋልመናል።

የመሟገቻዎቹ ሃሳቦች እጅግ በርካቶች ስለሆኑ ለማሳያነት የቆነጠርኩት ጥቂቶቹን ብቻ ነው። አጠቃላይ መንደርደሪያዬን እዚህ ላይ ገታ አድርጌ በራሴ የግል አመለካከት የራሴን አገር እውነታ ወደ መፈተሽ ልሸጋገር።

### ኢትዮጵያ ሆይ!

የአገሬን ወቅታዊ ችግሮች በስፋትና በወርዳቸው ልክ ዘርግቼ በማሕበራዊ የሂስ ጥበብ ለመፈተሽ ስሞክር ሁሌም የማርፍበት ዋነኛው ማጠንጠኛ አንድ ጉዳይ ነው - "እኔ ብቻ የሚል ግለኝነት።" ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ህመም መድኃኒቱ ያለው እኔ ዘንድ ብቻ ነው። የአገሪቱ ኢኮኖሚ መፍትሔው የሚቀመረው በእኔ የአእምሮ ማሽን ውስጥ ብቻ ነው። የማሕበራዊ ችግሮቻችን የሙቀትና የቅዝቃዜ መለኪያ ቴርሞ ሜትሩ የተያዘው በእኔ እጆች ብቻ ነው። የዕውቀትና የጥበብ ምሥጢራትን ቁልፍ በአደራ የተረከብኩት እኔ ብቻ ነኝ ወዘተ. የሚለው "የራስ ብቻ" የብቃት መፍትሔ ከአሁን ቀደምም ሆነ ዛሬ ምን ያህል የመከራ ዋጋ እያስከፈለን እንዳለ ያየነውና የምናየው እውነታ ነው። "እኔ ብቻ" እያሉ ራሳቸውን አሰላፊና ተሰላፊ ባደረጉ "የራስ ጣኦቶች" አማካይነት እነሆ የምንኖረውን ኑሮ እንድንኖር ተፈርዶብናል፤ ወይንም ፈርደውብናል።

ችግሩ በእኔነት ውስጥ ንፉግነት እንደሚስተዋል ይጠፋናል ማለት ባይቻልም፤ እኔ ብቻ የሚል ሰው "የእኔ ብቻ" የሚለውን በጎ ነገሮች ሁሉ አራግፎ ለመስጠትም እንደማይበረታ የታወቀ ነው። "እኔ" ብሎ መሽቀዳደም ለበጎ ሃሳብ ከሆነና መልካምነትን ለመጋራት መፍጠን ከሆነ እሰየው! ምን ገዶ! ችግሩ ያለው "እኔ ብቻ" ከሆነ የሚመዘዘው መዘዝ ተመጣጣኝ ዋጋ ስለሚጠይቅ ውጤቱ ይበልጥ የከፋ መሆኑ ላይ ነው።

መቼም ይህን መሰሉ ርእሰ ጉዳይ በዋነኛነት ደምቆ የሚሰበከውም ሆነ የሚነገረው አንድም በሃይማኖት ምስባኮች ላይ፣ ሁለትም ሙዚቃን፣ መጻሕፍትን፣ ሥዕልንና ቅርጻ ቅርጽን ወዘተ. አቅፎ በቤተኛነት በያዘው የኪነ ጥበባት ዘውጎች አማካይነት እንደሆነ አልጠፋኝም።

ለፖለቲካውና ለሥልጣን አላሚ ሠፈርተኞች ይህን መሰል መልእክት ከጆሯቸው ቢደርስም ፈጥነው እንደማይቀበሉት ይገባኛል። ስለዚህም የመጽሐፉን ደራሲ መሰል መልእክቶች የተላለፉባቸውን አንድ ሁለት የጥበብ ስራ ማጣቀሻዎችን ላስታውስ።

ተወዳጁ ነፍስ ሄር ደራሲያችንና መምህራችን ደበበ ሰይፉ "በትን ያሻራህን ዘር" የሚል አንድ ተወዳጅ ግጥም አለው። ይህ አጭር ግጥም አምቆ የያዘው መልእክት እጅግ የገዘፈ ብቻም ሳይሆን የመነሻችንን መልእክትም ለማጉላት ጥሩ ምሳሌ ስለሆነ እነሆ ግጥሙን አስታውሳለሁ።

**በንፕ በስርንጉጡ፣**
**በማጥ በድጡ**
**እንደ ተንጋለልክ - እንደ እንደ ዘመምክ**
**ትንፋሽህን እንደቋጠርክ**
**ልል ቀበቶህን እንዳጠበክ**
**የተልእኮህን አባዜ**
**የሕይወትህን ቃለ - ኑዛዜ**
**ወርውር!**
**የጅህን ዘገር።**
**በትን!**
**ያሻራህን ዘር።**
**ይዘኸው እንዳትቀበር።**

ይህ የመምህሬ ግጥም ከላይ ወደ ጠቀስኩት የመክብብ መጽሐፍ እንደገና እንድመለስ ግድ ይለኛል። የመጽሐፈ መክብብ ደራሲ ‹ጠቢቡ ሰለሞን› እንዲህ ይመክረናል። "ይህ ወይንም ያ ማናቸው እንዲበቅል ወይም ሁለቱም መልካም እንዲሆኑ አታውቅምና በማለዳ ዘርህን ዝራ፣ በማታም ጥረትህን አትተው።"

ነፍሰ ሄሩ የሙዚቃ ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠም በዚህን መሰሉ ርእሰ ጉዳይ ላይ ብዙ ዜማዎችን እንደተጫወተ እናስታውሳለን።

**"ስንት አየሁ ስንት ሰው ያሉ የነበሩ፣**
**ለመልካም ስራ እንጂ ለራስ የማይኖሩ፣**
**ከመቃብር በላይ ከታሪክ ኑባሪ፣**
**ስንት አየሁ ትልቅ ሰው ስንት አየሁ መሠሪ።**

ሃሳባችንን ወደመጠቅለሉ እንሂድ። ደራሲው ሄንሪም ሆኑ ሌሎች የጠቀስናቸው ጠቢባን የሚመክሩን አንድና ተመሳሳይ ጉዳይ እንድንከውን ነው። "ነገ! ነገ! እያልን እንዳንሞትና መክሊታችንን እንደተሸከምን እንዳንቀበር።" ዛሬ! አሁን! ለሕዝብና ለአገር በጎነት የሚበጀውን ተሽቀዳድመን እንድናሸጋግር እንጂ ለእምባና ለምሬት በሚዳርጉ ተግባራት ላይ እንዳንረባረብ።" የሁሉም ተማጽኖና የአደራ ቃል ይኼው ነው። ይህ ጸሐፊም ብእሩን ወክሎ በዓመታት ውስጥ ሲቃትት የኖረው ይህንኑ መልእክት ለማስታላለፍ ነው። **ሰላም ይሁን!**

> "የራስ ብቻ" የብቃት መፍትሔ ከአሁን ቀደምም ሆነ ዛሬ ምን ያህል የመከራ ዋጋ እያስከፈለን እንዳለ ያየነውና የምናየው እውነታ ነው። "እኔ ብቻ" እያሉ ራሳቸውን አሰላፊና ተሰላፊ ባደረጉ "የራስ ጣኦቶች" አማካይነት እነሆ የምንኖረውን ኑሮ እንድንኖር ተፈርዶብናል፤ ወይንም ፈርደውብናል።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## ገበያና ገበያተኛውን እያገናኙ ያሉት ኤግዚብሽንና ባዛሮች

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እየናረ የመጣውን ዋጋ ለማረጋጋት መንግሥት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ነው፤ እንዲያም ሆኖ ግን ችግሩ ቀጥሷል። ይህ ልጓም ያልተገኘለት የኑሮ ውድነት በአገር ውስጥ ብቻ የተከሰተ አይደለም፤ በተለይ በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም እየተስተዋለ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ህገወጥ ግብይት እየፈጠረ ያለው ችግር እንዳለ ሆኖ በአገሪቱ ከተከሰቱት የጸጥታና የመሳሰሉት ችግሮች ጋር በተያያዘ የኑሮ ውድነቱ እየጨመረ ይገኛል፤ ለእዚህ የኑሮ ውድነት ምክንያቱ አገራዊ ብቻ አይደለም። በአለም አቀፍ ደረጃ በሸቀጦች፣ በግብርና ምርቶች፣ ሎጂስቲክና ነዳጅ ላይ እየታየው ያለው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪም ችግሩ ይበልጥ እንዲባባስ እያደረገው ነው።

መንግስት ይህን የኑሮ ውድነት እያስከተለ ያለውን ጫና ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል፤ እየወሰደም ይገኛል። እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች መካከል ጤናማ የግብይት ሥርዓትን በማስፈን አምራችና ሸማቹን በቀጥታ ለማገናኘት የሚደረገው ጥረት አንዱ ነው።

ለዚህም ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው የታመነባቸውን የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከርና የተለያዩ ድጋፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ መንግስት መሰረታዊ ሸቀጦችን፣ የግብርና ምርቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግን ዋነው ጉዳይ አርጎ እየሰራ ነው፤ በተለይም በከተሞች የሚስተዋለውን የምርት አቅርቦት እጥረትና ህገወጥ ግብይት የወለደውን የግብይት ሰንሰለት መረዘምን ተከትሎ በሸቀጦች ዋጋ ላይ እየታየ ያለውን ንረት ለማረጋጋት ማህበራቱ ከመቼውም ጊዜ በተለየ በአሁኑ ወቅት የጎላ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አዘጋጅነት ለመጀመሪያ ጊዜ “ኅብረት ሥራ ለሰላምና ለተረጋጋ የገበያ ሥርዓት!” በሚል መሪ ቃል ሰሞኑን ለአራት ተከታታይ ቀናት የተካሄደው ከተማ አቀፍ የኅብረት ሥራ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየምም ይህንኑ ችግር መፍታትን ያለመ አንዱ መድረክ ነው።

መንግሥት ገበያን በማረጋጋት ኢኮኖሚውን ለመደገፍ እየወሰዳቸው ከሚገኙ እርምጃዎች መካከል በአዲስ አበባ ከተማ የምርት አቅርቦትን ለማሻሻል እና ተገቢ ያልሆነ ዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር ብሎም በንግድ ስርዓት ውስጥ ተንሰራፍቶ የቆየውን የደላላ ሰንሰለትን ማቋረጥ ትልቁ ሥራ ነው። ለዚህም በአገሪቱ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ገንቢ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል።

በአዲስ አበባ ኤግዚብሽን ማዕከል ከግንቦት 18 እስከ 21 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄደው ኤግዚቢሽንና ባዛር ያገኘናቸው ሸማቾችም መሰል ኤግዚቢሽንና ባዛሮች መዘጋጀታቸው ገበያውን ለማረጋጋት የሚኖራቸው ሚና የጎላ መሆኑን ይናገራሉ።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ አዲሱ ገበያ ነዋሪው አቶ ዳዊት አስፋው በኤግዚብሽን ማዕከሉ ተገኝተው ግብይት ፈጽመዋል። አቶ ዳዊት ኤግዚብሽንና ባዛርን ጨምሮ በተለይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉበት ቦታ የተሻለ የገበያ ሁኔታ ስለመኖሩ ይናገራሉ። በዚህ ገበያ የሚቀርቡ ሁሉም ምርቶች ውጭ ካለው የገበያ ዋጋ እጅጉን የተሻለ ዋጋ እንዳላቸው ይገልጸሉ።

ማር እየሸመቱ ያገኘናቸው አቶ ዳዊት ከአምስት ወራት በፊት በዚሁ ቦታ የከፋ ቦንጋ ማር መግዛታቸውን ያስታውሳሉ። ማሩ ንጹህ እና ዋጋውም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ይናገራሉ። እንዲህ ባሉ ገበያዎች ጥራት ያለውና ትኩስ ምርት ከማግኘት ባለፈ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት ይቻላል ነው የሚሉት።

አቶ ዳዊት በዕለቱም አንድ ኪሎ የቦንጋ ነጭ ማር በ260 ብር እና አምስት ኪሎ የበቆሎ ዱቄት በ140 ብር ከሃምሳ ሳንቲም ገዝተዋል፤ ይህም ውጭ ካለው ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነት እንዳለው አንስተው ሌሎች ምርቶችንም ለመሸመት ዝግጁ እንደሆኑ አጫውተውናል።

የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት በኩል የኅብረት ሥራ ማህበራት ትልቅ ድርሻ አላቸው የሚሉት አቶ ዳዊት፣ ማህበራቱ ከዚህ በበለጠ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በሚፈለገው መጠን ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል ሲሉም ያስገነዝባሉ። ‹‹እንዲያውም ዘርፉ ሕብረተሰቡ በሚፈለገው መጠን አልተሠራበትም፤ ሊሠራበት ይገባልም›› ብለዋል።

ማህበረሰቡም ማኅበራቱ ባሉበት ቦታ ሁሉ በመሄድ መግዛት ከቻለ የማኅበራቱን አቅም ማጎልበት ያስችላል። አገልግሎታቸውንም በስፋት ለማቅረብ ያስችላቸዋል። መንግሥትም እነሱን በማጠናከርና በመደገፍ ለህበረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ መሥራት አለበት። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል የተጀመረው የእሁድ ገበያ አንዱ አማራጭ እንደመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

በቋሚነት ከዘለቀው የእሁድ ገበያ በተጨማሪ በተለያየ ጊዜ የሚዘጋጀው ባዛርና ኤግዚቢሽንም እንዲሁ ብዙ ሳይቆይ በአንድ ወር አልያም በሁለት ወራት ቢከፈት ገበያውን ማረጋጋት ያስችላል ያሉት አቶ ዳዊት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ገበያዎች አሉ ከተባለ የትም ይሁን የት ይሄዳሉ። ባይገዙም ቦታው ድረስ በመሄድ ሁኔታውን መመልከት ያስደስታቸዋል፤ ይህ በራሱ ጥሩ ነገር እንደሆነ በመግለጽ ሌሎችም ይህን ቢያደርጉ ይጠቀማሉ ይላሉ።

የአቶ ዳዊትን ሀሳብ የሚጋሩት ወይዘሮ ሀና ማሙዬ በበኩላቸው የህብረት ሥራ ማህበራቱ የተለያዩ ምርቶችን ይዘው በአንድ ቦታ ላይ መገኘታቸው በራሱ ጥሩ እንደሆነ በመግለጽ ገበያውንም ማረጋጋት እንደሚችሉ ይናገራሉ። ምንም እንኳን እርሳቸው ለኤግዚብሽን ማዕከሉ ቅርብ ከሆነው መሿለኪያ የመጡ ቢሆንም ሩቅ ያሉትም ቢሆኑ ተመሳሳይነት ካለው የእሁድ ገበያ መጠቀም እንደሚችሉ ይጠቁማሉ።

በወቅቱ አንድ ኪሎ ኮረሪማ በ100 ብር ሲገዙ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሀና፤ በተለይም የጤፍ ዋጋ ውጭ ካለው የተሻለ እንደሆነ ነው የሚናገሩት። ውጭ ላይ በኪሎ ከ50 ብር እስከ 54 ብር የሚሸጠው ጤፍ ከ44 እስከ 46 ብር እየተሸጠ መሆኑን ገልጸዋል።

በዘይት ዋጋ ላይ ብዙ ልዩነት እንደሌለም ተናግረው፣ ገበያው ላይ መገኘቱ በራሱ ትልቅ ነገር ነው ይላሉ። ውጭ ላይ ከአንድ ሺ ብር በላይ የሚሸጠው ከውጭ የሚገባ ዘይት አለ። ነገር ግን በአገር ውስጥ የሚመረተው ኮከብ የሚባል የኑግ ዘይት በ870 ብር መግዛታቸውን ይናገራሉ፤ መንግሥት ይህን አማራጭ ማቅረቡ መልካም እንደሆነ ገልጸው፤ ‹‹የሆነ ሆኖ ዋናው ጤፍ ነው እሱ ብቻ አይጥፋብን ሌላው ትርፍ ነው›› ይላሉ።

በኤግዚብሽን ማዕከሉ እርሳቸው ያሉት ጤፍም ይሁን ነጩ፣ ከቀዩ፤ መካከለኛው ከሠርገኛው በዓይነት በዓይነቱ ገበያው ላይ ቀርቧል፤ አጠቃላይ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን እንዲሁም የእጅ ሥራ የሆኑ የሸክላ ውጤቶችም ለገበያ ቀርበዋል። በግቢው ውስጥ ለአይን የሚማርኩ ትኩስ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ጨምሮ ጥራጥሬዎችም እንዲሁ በገበያው በስፋት ይታያሉ።

የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከሆኑት መካከልም የንጽህና አገልግሎት መስጫ የሆኑ ደረቅና ፈሳሽ ሳሙናዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረባቸውን ተመልክተናል። ለአብነትም ውጭ ላይ ከ300 ብር በላይ የሚሸጠው አምስት ሊትር የልብስ ሳሙና ከ200 እስከ 250 ብር ሲሸጥ ደረቅ ሳሙና ደግሞ ከ26 ብር ጀምሮ ሲሸጥ ነበር።

ከደቡብ ምዕራብ ከፋ ዞን ከከፋ ጫካ ማር ዩኒየን የመጡት የቦርድ ሰብሳቢ አቶ በዛብህ በቀለ ማርና ኮረሪማ ይዘው ቀርበዋል። ዩኒየኑ 34 ማህበራት ያሉትና ዘጠኝ ሺ አርሶ አደሮችን ያቀፈ መሆኑን በመግለጽ ዩኒየኑ ማርና ኮረሪማን በስፋት እያመረተ ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያም ማቅረብ እንደቻለ ይናገራሉ።

በ2013 ዓ.ም ማር ወደ ጀርመን ልኳል፤ በአሁኑ ወቅት ግን በአገር ውስጥ ማር በከፍተኛ መጠን እየተፈለገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማሩን ለአገር ውስጥ ገበያ ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ይገልጸሉ። ይሁንና በተለይም አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በተለያዩ የክልል ከተሞች በስፋት ተደራሽ ለማድረግ የገበያ ቦታ ችግር መሆኑን አቶ በዛብህ ጠቅሰዋል።

ለአራት ቀናት ያለምንም ክፍያ በኤግዚብሽን ማዕከሉ ምርቶቻቸውን ለገበያ ማቅረብ እንዲችሉ መደረጉ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን በመግለጽ፤ ከሽያጩ ባለፈ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ጥሩ አጋጣሚ እንደፈጠረላቸውም ይናገራሉ። ከዚህ ቀደምም ባገኙት ዕድል በቀጥታ ሸማቹን ከማግኘት ባለፈ ሰፊ የገበያ ትስስር መፍጠር መቻላቸውን ይናገራሉ።

የአካባቢውንና የወቅቱን ገበያ በማየት ቦርዱ በወሰነላቸው መሠረት አንድ ኪሎ ማር 260 ብር እንዲሁም አንድ ኪሎ ኮረሪማ በ100 ብር እየሸጡ መሆኑን የገለጹት አቶ በዛብህ፤ በዚህም ሸማቾች ተጠቃሚ እንደሚሆኑና ገበያውንም ማረጋጋት እንደሚቻል ይጠቅሳሉ። በባዛሩ ላይም አስር ኩንታል ማር እና ሶስት ኩንታል ኮረሪማ ይዘው ቀርበዋል።

ለገበያው ይዘው ከቀረቡት የምርት መጠን በላይ በባዛር ገበያው ኮረሪማ ወደ ውጭ ገበያ የሚያቀርብ ላኪ ያገኙ ሲሆን 10 ኩንታል የተፈለፈለ ኮረሪማ እንዲቀርብለት በጠየቀው መሰረት ለማቅረብ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተስማምተው ውል አስረዋል። ለዚህም የቅድመ ዝግጅት ሥራውን ከወዲሁ መጀመራቸውን እና እንዲህ አይነት መድረኮች በተለይም የገበያ ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው ብለዋል።

የይርጋጨፌ ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበር የተቆላ ቡና ክፍል ኃላፊ አቶ አሻግሬ አድማሱ በበኩላቸው በባዛሩ ላይ የተቆላ ቡና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቾች ይዘው መቅረባቸውን ገልጸዋል። በመሆኑም በኤክስፖርት ደረጃ ተቆልቶ የተፈጨ አንድ ኪሎ ቡና 460 ብር ይዘው ቀርበዋል። ይህም ውጭ ላይ ከ570 ብር በላይ የሚሸጥ ነው።

የቡና ልማቱ በይርጋጨፌ ከሚገኙ አርሶ አደር አባላት የሚገኝ እንደሆነ የገለጹት አቶ አሻግሬ፤ በልማቱ ላይ ብቻ ከ40 ሺ በላይ አርሶ አደሮችን ያቀፈ ማኅበር መሆኑን ጠቅሰዋል። ከአርሶ አደሩ የተቀበሉትን ቡናም ቃሊቲ ማሰልጠኛ አካባቢ በሚገኘው ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ቆልተው፣ ፈጭተውና አሽገው ለገበያ ያቀርባሉ። ይሄው ቡና ሂልተን ሆቴልን ጨምሮ በተለያዩ ሆቴሎችና ሱፐርማርኬቶችና ሆቴሎች ላይ ይገኛል።

በቋሚነት ካለው ገበያ በተጨማሪ በእንዲህ አይነት የባዛር ገበያ ላይ መሳተፍ መቻላቸው ሰፊ የገበያ ዕድል የሚፈጥርላቸው መሆኑን አቶ አሻግሬ ይገልጻሉ። ይህ ብቻ አይደለም፤ በቀጥታ ሸማቹን ማግኘት የሚቻልበት መሆኑን ይናገራሉ። በተለይም በአሁኑ ወቅት ካላው የኑሮ ውድነት አንጻር ለውጭ ገበያ ከሚያቀርቡበት ዋጋ ባነሰ እያቀረቡ መሆናቸውንም ገልጸው፣ ይህም ኅብረተሰቡን ለመጥቀም እንዲሁም ቡናውን ለማስተዋወቅ ጭምር ትልቅ ዕድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።

‹‹የኅብረት ሥራ ማህበራት ችግር ፈቺና መፍትሔ መሆን የሚችሉ ናቸው፤ ለዚህም በጋራ መሥራትና ማገር ያስፈልጋል›› ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ዓሊ፤ ሰው ሰራሽ የሆነውን የኑሮ ውድነት ለማርገብና የተረጋጋ ገበያ ለማስፈን ታልሞ የተዘጋጀ ኤግዚብሽንና ባዛር መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ሃላፊው ገለጻ፤ ከአቅርቦት ጋር ያለውን ችግር ለመቅረፍም ከአርሶ አደሩ ጋር በመቀናጀት ሰፋ ያለ ውይይት በማድረግ ችግሩን መለየት ተችሏል። ለዚህም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለተረጋጋ ገበያ መፍትሔ እንዲሆኑ እየተሠራ ነው። ከእሁድ ገበያ ባሻገር እንዲህ አይነት መድረክ ያለውን ፋይዳ በመረዳትም ከተማ አስተዳደሩ ለኅብረት ሥራ ኤጀንሲው አንድ ቢሊዮን ብር መድቧል።

በመሆኑም ጤፍና የስንዴ ዱቄትን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶች በባዛሩ በስፋት መግባታቸውን የገለጹት አቶ ግዛቸው፤ ምርቱን ከስር ከስር እየተተካ እንደሆነና ቀጣዩን ክረምትም ሊያዘልቅ እንደሚችል ነው ያነሱት። አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ሌሎች ምርቶችን ደግሞ ከክልል አርሶ አደሮች ጋር በመነጋጋር ለማቅረብ አተየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

በኤግዚብሽንና ባዛሩ ላይ ከከተማዋ ውጭ ከስድስት ክልሎች የመጡና በተለያየ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፎች የተደራጁ እንዲሁም ከኅብረት ሥራ ዘርፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ተቋማት ተገኝተዋል። በማህበራቱ መካከልም የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣ የገንዘብ ብድር ቁጠባና የኅብረት ሥራ ግንዛቤ እጥረቶችን መቅረፍ፣ ዘላቂነት ያለውን የገበያ ትስስርና መስተጋብር ለመፍጠር እንዲሁም የማኅበራቱን ገጽታ የመገንባት ዓላማ ያለው መሆኑ ተጠቁሟል።

በአራት ቀናትም 178 የኅብረት ሥራ ማህበራትና የተለያዩ ተቋማት እንዲሳተፉ በማድረግ ከ456 ዓይነት በላይ የምርት አይነቶችን በማቅረብ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና አገልግሎትን በማስተዋወቅ ከ4 ሺ 656 ኩንታል በላይ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም የዕደ ጥበብ ውጤቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ሽያጭ ማከናወን እንደተቻለና በዚህም 27 ሚሊዮን 912 ሺ 755 ብር እንደተገኘ በመዝጊያ ስነስርዓቱ ላይ የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

> “ሰሞኑን በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማእከል ለአራት ቀናት በተካሄደው ኤግዚቢሽን 178 የኅብረት ሥራ ማህበራትና የተለያዩ ተቋማት ተሳትፈዋል፤ ከ456 ዓይነት በላይ የምርት አይነቶችም ቀርበዋል። የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርትና አገልግሎትን በማስተዋወቅ ከ4 ሺ656 ኩንታል በላይ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም የዕደ ጥበብ ውጤቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ሽያጭ ማከናወን ችለዋል፤ በዚህም 27 ሚሊዮን 912 ሺ 755 ብር መገኘቱን በመዝጊያ ስነስርዓቱ ላይ የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።”

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ጥሉብን...የተወደደ እንወዳለን

**ዋለልኝ አየለ**

አንድ አብሮ አደግ ጓደኛ አለኝ፤ ከዚህ ጓደኛዬ ጋር ብዙ ጊዜ ነው የምንጨቃጨቀው። የምንጨቃጨቅበትን ምክንያት ልንገራችሁና ማን ትክክል እንደሆነ ፍረዱ።

ምግብ ለመብላት ወይም አንድ ሁለት ለማለት ስንገባ፤ አዲስ ቤት ከሆነ ዋጋ ይጠይቃል። እኔ ደግሞ በመጠየቁ እናደዳለሁ። ‹‹ፋራ ነህ እኮ! ቢያንስ ‹ሜኑ አምጡልኝ› ይባላል እንጂ እንዴት የእያንዳንዱን ምግብ ዝርዝር እየጠራህ ዋጋ ትጠይቃለህ?›› እያልኩ እናደድበታለሁ።

እሱም በበኩሉ ፋራው እኔ እንደሆንኩ በቁጣ ይወርድብኛል። ዋጋ መጠየቅን የመሰልጠን ምልክት ነው የሚያደርገው፤ የምግብና መጠጥ ዋጋ ዝርዝሩን አያምነውም፤ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየዕለቱ ዋጋ ስለሚጨምር ወቅታዊ መረጃ አይኖረውም ብሎ ነው የሚያምን። በዚያ ላይ የምግብ ዝርዝሩ ላይ ያሉት ምግቦች ስለማይኖሩ፤ በቀጥታ ያለውን ጠይቆ አስተናጋጇ ስትነግረው እዚያው ላይ እያከታተለ ዋጋውን ይጠይቃል። እኔ ደግሞ ‹‹አስፎገረኝ›› በሚል ስሜት እንደማፈር ብየ ትኩረቴን ወደሌላ አደርጋለሁ።

በነገራችን ላይ ይህን የሚያደርገው ሲጋብዝ ብቻ አይደለም፤ ሲጋበዝም ጭምር ነው። ‹‹የትኛውም ሀብታም ይጋብዘኝ፤ አይገባውም የምለው ቤት ውስጥ የተጋነነ ዋጋ መክፈል የለበትም›› ነው የሚል። ዋጋውን ካላመነበት ካልወጣን ይላል።

ለዚህ ትዝብት መነሻ የሆነኝ ባለፈው ቅዳሜ (ግንቦት 20) ይህ ጓደኛዬ እራት እንብላ ብሎኝ ካራ አካባቢ ከአንድ ቤት ገብተን ነው። በእውነቱ የገባንበት ቤት ያን ያህል ትልቅ የሚባል ቤት አይደለም፤ በየመንገዱ ከሚገኙት አነስተኛ ሆቴሎች አንዱ ነው።

ከአንድ ውጪም ውስጡም ሰው የበዛበት ሆቴል ገብተን እንደተቀመጥን አስተናጋጇ መጥታ በትህትና ‹‹ምን ልታዘዝ›› አለችን። የሚበላ ጠይቅናት ያሉትን ምግቦች ነገረችን። ይሄው ልማደኛ ጓደኛዬ እንደልማዱ ዋጋ ጠየቀ። ለአንድ ምግብ ዝቅተኛ የሚባለው ዋጋ 170 ብር ነው። በፍጹም እዚህ ቤት ውስጥ በዚህ ዋጋ አንበላም ካልወጣን አለ፤ እኔም እንደተለመደው በ‹‹እንፎገራለን›› ስሜት ብለማመጥ ሊሰማኝ አልቻለም፤ ትቶኝ ተነሳ። እኔም ተነሳሁ። በዙሪያችን የነበሩ ሰዎች አተያይ የግርምትና የትዝብት ነበር። ‹‹ምን አይነት ፋራዎች ናቸው›› እያሉ ይሆናል።

እዚያ ቤት ውስጥ ዝቅተኛ ዋጋ 170 ብር መሆኑን ካየሁ ወዲህ ግን ያ ጓደኛዬ ትክክል መሆኑን አመንኩ። እውነትም እኔ ነበርኩ ፋራ። እንደዚህ አይነት መረን የለቀቀና ይሉኝታ የለሽ ቤት ውስጥ ይሉኝታ አያስፈልግም። የፈለጋቸውን ይበሉ ጥሎ መሄድ መብት ነው። የውሃ መድፊያ የሌለው መጸዳጃ ቤት ይዘው እኮ ነው በዋጋ መቆለል ብቻ የቤታቸውን ደረጃ ከፍ ያደረጉ የሚመስላቸው።

አዲስ አበባ ውስጥ አንድ የሚገርመኝ ነገር፤ አንድ አካባቢ ባሉ ቤቶች በተመሳሳይ ደረጃና በተመሳሳይ የምግብ ጥራት ላይ ሆነው የዋጋ ልዩነታቸው ግን በተለምዶ ‹‹ማዘር ቤቶች›› የሚባሉት ውስጥ ምሳ ያበላል።

ብዙ ጊዜ እንደምናስተውለው የዋጋ ልዩነት የሚታየው በቤቶች ደረጃ እንጂ በምግብ ይዘት ልዩነት አይደለም። እርግጥ ነው ትልቅ ደረጃ ያለው ቤት ሲገነባ ብዙ ወጪ አስወጥቷል፤ የኪራይ ከሆነም ኪራዩ ውድ ነው የሚሆን። ይህ ስለሚታወቅ መሰለኝ ትልቅ ደረጃ ያለው ቤቶች ውስጥ የዋጋ መወደድ ብዙም አይገርምም።

ግን የቤቱ ማሽብረቅ ለተመጋቢው ምን ጥቅም አለው? ወደ ሰውነቴ የሚሄደው የቤቱ ቀለም ነው ወይስ ምግቡ ነው? ይህን ያልኩበት ምክንያት በትልልቅ ቤቶች ውስጥ የምግቡ መጠን አነስተኛ ስለሚሆን ነው። ጥብስ አዘህ፤ በትንሽ ሳህን መረቅ ይሞላና በዚያ መረቅ ውስጥ የሚዋኙ ቲማቲምና ሽንኩርት እና አንዳንድ ሥጋዎች ናቸው። እነዚህ ቤቶች ግን በደረጃቸው ልክ የሚመጥን ምግብ ቢያቀርቡ ለቤታቸው ክብር አይሻልም ነበር ወይ?

በነገራችን ላይ ይሄ ነገር የአገልግሎት ሰጪዎች ብቻ ሳይሆን የተጠቃሚውም ችግር ነው። የተወደደ ነገር እንወዳለን። ‹‹ሐበሻ የረከሰ አይገዛም›› የሚባል አባባል አለ። ደረጃው ከርካሽ ዕቃዎች በታች ቢሆን እንኳን የተወደደ ነገር ነው የምንወድ። ‹‹ክብር›› የምንለው ነገር አለ። በምንጠቀመው ዕቃ ወይም በምንመገበው ምግብ መጠንና ጥራት ሳይሆን በቤቱ ደረጃና በዋጋው ውድነት ነው ክብራችንን የምንገልጸው።

ከአራት ይሁን አምስት ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ‹‹እሁድ መዝናኛ›› ፕሮግራም ላይ ያየሁት ትዝ አለኝ። ‹‹ታዋቂነት እና መዘዙ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነበር። ታዋቂ ሰዎች ታዋቂ በመሆናቸው የሚገደቡትን ገደብ እየተናገረ ነበር።

አርቲስት ሥዩም ተፈራ መንገድ ዳር የሚሸጥ ፓስቲ በጣም እወዳለሁ አለ። ይህን ፓስቲ ግን በነፃነት መብላት አይችልም ነበር። ሲበላ ያየው አላፊ አግዳሚ ሁሉ በግርምት ይመለከተዋል። በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ፓስቲ የሚበላው በምርጫና በፍላጎት ሳይሆን በድህነት ነው። አርቲስት ሥዩም ምን ቸገረኝ ብሎ ነው ፓስቲ የሚበላ እያሉ ነው። እነዚህ ሰዎች ከባባድ የሥጋ ምግቦች መዘወተር እንደሌለባቸው ሐኪሞች የሚሉትን እንኳን ሰምተው አያውቁም ማለት ነው። አርቲስት ሥዩም አርቲስት ስለሆነ ብቻ ከሳምንት ሳምንት ከዕለት ዕለት ቁርጥ፣ ፒዛ፣ በርገር.... ሊበላ አይችልም። ለጤናም የሚመከረው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ያሉ ምግቦችን መቀያየር ነው።

በተመሳሳይ ሌሎች ታዋቂ ሰዎችም በዚያ ፕሮግራም ላይ ሲናገሩ የነበረው አነስተኛ ቤቶች ውስጥ ሲገኙ ብዙ ሰው በግርምት ይመለከታቸው እንደነበር ነው። በእውነቱ ይሄ ኋላቀር አስተሳሰብ ነው ሊባል የሚችል። አንድ ሰው ሀብታም ስለሆነ ብቻ ባለኮከብ ሆቴል ብቻ እየመረጠ ሊሄድ አይችልም። በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጁና በአነስተኛ ቤቶች ውስጥ ያሉ ምግቦችም ያስፈልጉታል።

በተለምዶ ‹‹ማዘር ቤቶች›› የሚባሉ ምግብ ቤቶች አሉ። በአዲስ አበባ በአንዳንድ ጎዳናዎች ዳርቻ የምናያቸው የኮንቴነር ቤቶች ማለት ነው። ለምሳሌ አምስት ኪሎ ከየካቲት 12 ሆስፒታል ጀርባ ያሉት። እነዚህ ቤቶች ውስጥ የሚሰራ ፍርፍር እና ሽሮ ባለአምስት ኮከብ ሆቴል ውስጥ ከሚሰራ ሽሮ የበለጠ ይጣፍጣሉ። ምክንያቱም አሰራራቸው ለአብዛኛው ሀበሻ ቅርብ ነው።

ዳሩ ግን እነዚህ ቤቶች ውስጥ መታየት የችግር ማሳያ ስለሚመስላቸው ብዙ የማይገቡ ሰዎች ይኖራሉ። ስነ ልቦናም ጭምር ነው። ለምሳሌ፤ ከአንድ አይነት ግብዓት፣ በአንድ የምግብ አዘጋጅ፣ አንድ ቦታ ተዘጋጅቶ፤ አንደኛው ወደ ትልቅ ሆቴል፣ አንደኛው ደግሞ መንገድ ዳር ወዳለች ትንሽ ቤት ተወሰደ እንበል። ለአንድ ቀብራራ ነኝ ባይ ሁለቱንም አቅምሶ ‹‹የትኛው ይሻላል›› ቢሉት ትልቅ ሆቴል ውስጥ ያለውን ሊመርጥ ይችላል።

መነሻዬ ከአንድ አነስተኛ ሆቴል ውስጥ ያየሁት የዋጋ መጋነን ነው። ምንም እንኳን የዋጋ መጋነን በአገር አቀፍ ደረጃ አጀንዳ ቢሆንም፤ ዳሩ ግን እኛም ቀብራራነቱን እናበዛዋለን። የተወደደ ነገር ነው ትልቅ የሚያደርገን የሚመስለን። መለኪያችን የምንመገበው ምግብ ወይም የምንገለገልበት ዕቃ ጥራት እንጂ የዋጋው ውድነት መሆን የለበትም!

# ዓለም አቀፍ




## የዝንጀሮ ፈንጣጣ "በመካከለኛ" ደረጃ የዓለም የጤና ሥጋት መሆኑ ተገለጸ

አዲስ አበባ፣ የዝንጀሮ ፈንጣጣ በመካከለኛ ደረጃ የዓለም የጤና ሥጋት መሆኑን የዓለም ጤና ድርጅት ገለጸ።

ቫይረሱ ሥጋት ሊሆን የሚችለው ለከባድ በሽታ ተጋላጭ ወደሆኑ ሕፃናት ከተዛመተ እና የበሽታ መከላከል አቅማቸው ወደተዳከመ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከተሠራጨ መሆኑን የዓለም ጤና ድርጅት አመላክቷል።

ከፈረንጆቹ ግንቦት 26 ጀምሮ 23 አገራት በድምሩ 257 በዝንጀሮ ፈንጣጣ ቫይረስ የተያዙ ሰዎችን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፥ 120 ሰዎች ደግሞ በቫይረሱ ሳይያዙ አልቀረም የሚል ጥርጣሬ እንዳለ ድርጅቱ በመግለጫው አስታውቋል።

በቫይረሱ እስካሁን የተመዘገበ የሞት አደጋ የለም።

የዓለም ጤና ድርጅት የዝንጀሮ ፈንጣጣ ወረርሽኙ ከዚህ ቀደም ተከስቶባቸው በማያውቁ አገራት ሳይቀር በአንድ ጊዜ መታየቱ በሽታው መከሰቱ ሳይታወቅ ተደብቆ መቆየቱን እንደሚያሳይ አመላካች ነው ብሏል።

እንደ ድርጅቱ ገለጻ ቫይረሱ ተላላፊ በመሆኑ እስካሁን ባልታየባቸው አገራትም በቀጣይ ሊከሰት እንደሚችል ጠቁሞ የሚያሰጋ ገዳይ በሽታ ባለመሆኑ ሰዎች ሳይጨነቁ በተቻለ መጠን ራሳቸውን ከንክኪ በማራቅ የግል ንፅሕናቸውን እንዲጠብቁ ማሳሰቡን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል።



## የሱዳን ወታደራዊ መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማንሳቱን አስታወቀ

አዲስ አበባ፣ የሱዳን ወታደራዊ መንግስት በአገሪቱ በተከሰተው አለመረጋጋት ምክንያት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማንሳቱን አስታውቋል።

የሱዳን ወታደራዊ መንግስት መሪ ጀኔራል አብዱል ፈታ አልቡርሃን በሰጡት መግለጫ ባለፈው ዓመት ጥቅምት 25 በወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ስልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳ ማዘዛቸውን ገልፀዋል።

የሱዳን ሽግግር ሉዓላዊ ምክር ቤት በበኩሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማንሳት የተወሰነው በሽግግሩ ወቅት በአገሪቱ የተፈጠረው ውጥረት እንዲረግብ እና ውይይቶችን ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር መሆኑን አመላክቷል።

የአገሪቱ የፀጥታ እና የመከላከያ ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳቱን ተከትሎ በእስር ላይ የሚገኙ ሱዳናውያን በሙሉ ከእስር እንዲፈቱ ሃሳብ ማቅረቡ ነው የተገለጸው።

በዚህም 125 እስረኞች ከበርካታ ወራት የእስር ጊዜ በኋላ መፈታታቸውን ሱዳን ትሪቡን በዘገባው አመላክቷል።

በሱዳን ከመፈንቅለ መንግስት በኋላ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ለማርገብ በተወሰዱ እርምጃዎች እስካሁን ከ100 በላይ ሱዳናውያን ለህልፈት መዳረጋቸውን የሬውተርስ ሱዳን ትሪቡን ዘገባ ያመላክታል።

# ባለውለታዎቻችን

## የሥነጽሑፍ ምርትን፤ ማሕበረ-ባህላዊ እሴት ተከላን፤ ትውልድ ቀረፃንና አገር ግንባታን በ'ሱ አየሁት

**ግርማ መንግሥቴ**

የገዘፈ ሰብእና ያላቸው ሰዎች በተደጋጋሚ ሊነሱ የሚችሉባቸው ምክንያቶች አያሌ ሲሆኑ፤ የዛሬው እንግዳችንም የዚሁ ሰብእና ተጋሪ ናቸው። ሁለገብ ሰብእና ያላቸው ሰዎች ሊታወሱ የሚችሉባቸው ስራዎቻቸው በርካታ ሲሆኑ ከእነዚህም አንዱ የሕይወት ዘመናቸውን በደራሲነት፣ ጋዜጠኝነት፣ ተርጓሚነትና በሌሎችም የሙያ ዘርፎችና መንግሥታዊና ማህበራዊ ሃላፊነቶች ያሳለፉትና በዋግ አውራጃ (የወሎ ክፍለ አገር) የተወለዱት ማሞ ውድነህ ናቸው። (የተወለዱበትን አመት ምህረት አልፎ አልፎ የተለያየ ሆኖ ይገኛል፤ በመሆኑም ማጣራትን ይፈልጋል። እዚህ የተጠቀሰው አብዛኛዎቹ ምንጮች የተጠቀሙበት ነው።)

ሥራዎቻቸው በስለላ፣ በታሪክ፣ በልቦወለድና ተውኔት ላይ የሚያተኩሩት፤ በ1954 የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን፤ "ሁለተኛው የዓለም ጦርነት" በሚል ርእስ (የመጨረሻቸው "የደረስኩበት" የሚለው ግለ-ሕይወት ታሪካቸው ነው) የደረሱትን ማሞ ውድነህ (1923 እስከ 2004 ዓ.ም) በኢትዮጵያ የድርሰትና አጻጻፉ ዓለም ክብረወሰኑን የያዙ ሲሆን፤ ይህም ሊሆን የቻለው በእስከ ዛሬው የአገራችን የድርሰት ዓለም ያልተደፈረው የ59 መጻሕፍት (የሰሯቸውን ስራዎች በተመለከተ ከ53 እስከ 59 ባሉት ቁጥሮች መካከል የሚዋዥቁ መረጃዎች ናቸው ያሉት። ይህ ጽሑፍ፣ በእንግሊዝኛ የጻፏቸውም ስላሉ፣ ከፍተኛውን ቁጥር መውሰድን መርጧል) ደራሲና ተርጓሚ በመሆናቸው ሲሆን፤ ይህም እስከ አሁን ሳይደፈር ባለበት ይገኛል።

የጋዜጠኛ ማሞ "አዲስ ዘመን" ፣ "ፖሊስ እና እርምጃው"፣ "ህብረት" እና "የዛሬይቱ ኢትዮጵያ" ጋዜጦች ላይ መስራታቸውን ልብ ይሏል፤ ስራዎች በጥቅሉ ሲገለፁ ይሰማል እንጂ በአብዛኛው በስም የሚታወቁ አይደሉም። በመሆኑም፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እያዋዛን የምንጠቅስላቸው መጻሕፍት በሙሉ የማሞ ሲሆኑ፤ የመጀመሪያዎቹ አስሩ - ሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ የሴቷን ፈተና፣ ከወንጀለኞቹ አንዱ፣ ቬኒቶ ሙሶሊኒ፣ የገባር ልጅ፣ ሁለቱ ጦርነቶች፣ አደገኛው ሰላይ፣ ዲግሪ ያሳበደው፣ ካርቱም ሔዶ ቀረ?፣ እና የ፷ቱ ቀን ጦርነት ስለመሆናቸው ለመናገር ጋዜጠኞች ሳንቀር ስንቸገር ይታያል።

ለአስራ ሁለት አመታት የኢትዮጵያ ደራሲዎች ማኅበርን በሊቀ-መንበርነት የመሩት ማሞ ከደራሲና ጋዜጠኝነትም በላይ የሚዲያ ተቋም እስከ ማደራጀት ድረስ የዘለቀ አቅም የነበራቸው ሰው ነበሩ። ከዚሁ አኳያም፣ በአንድ ወቅት "አዲስ ዘመን እያለሁም የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ የነበሩት ጄነራል ጽጌ ዲቡ ለንጉሱ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ፖሊስና እርምጃው ጋዜጣን እንዳቋቁም ታዘዝኩ።" ማለታቸው የሚታወስ ሲሆን፤ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ፕሬስ መምሪያን እንዲያቋቁሙ ወደ አስመራም መላካቸውን መናገራቸውም ይታወሳል።

የሃይማኖት ኮሚቴ ውስጥ በመሳተፍ በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ሰላምን ለማምጣት ጥረት ካደረጉት ጎምቱዎች መካከል አንዱ የሆኑት ማሞ ውድነህ በስራዎቻቸው ሁሉ ማለት በሚባል ደረጃ ለአገርና ሕዝብ አንድነት ልዩ ትኩረትን ሰጥተው ይሰሩ (ይደርሱ) የነበረ ሲሆን፤ እሱም ስለማህበራዊ ኖሮ (ለማህበራዊነት)፣ ስለአብሮነት፤ ስለመረዳዳት፤ በተለይም በማህበረ-ባህላዊ እሴቶች ላይ ሲሰሩ የነበር።

ማሞ ከላይ በጠቀስንላቸው የትኩረት ነጥቦች ላይ በሚገባ ብዕራቸውን የሰነዘሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ ሥነ ጽሑፋዊ ምርቶቻቸውም መካከል "እድርተኞቹ"፣ "እቁብተኞቹ፣" "ማህበርተኞቹ" ... የሚሉት ቀዳሚ ተጠቃሾች፤ ከሌሎቹም በብዛት የሚታወቁላቸው ናቸው።

በእስከዛሬው የአገራችን የድርሰትና ጸሐፍት ዓለም ውስጥ ማንም ደራሲ የማሞ ውድነህን ያህል ለማህበረ-ባህላዊ እሴት ልዩ ትኩረትን ሰጥቶ ስራዎቹን ለንባብ ያበቃ ደራሲ ይህ ጸሐፊ አያውቅም፤ ነካ ጣል ነካ ጣል ካልሆነ በስተቀር። ይህም፣ ከላይ እንዳልነው ማሞን ከሌሎች ለየት ይሉ ዘንድ ያስገድዳልና ዛሬ እዚህ ስለመነሳታቸው፤ በተደጋጋሚው ስለመዘከራቸው አንዱ ምክንያት ነው። በተለይ፣ በዚህ በአሁኑ፣ ሁሉ ነገር ችግር ባለበት ዘመን፣ እነዚህ ሶስት መጻሕፍት ተደግመውና ተደጋግመው ሊነበቡ የሚገባቸው መሆናቸውን ሳይጠቅሱ ማለፍ ሀላፊነትን መዘንጋት ነው የሚሆነውና ሶስቱ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ አንጡራ እሴትና አገር በቀል እውቀት ላይ የተመሰረቱ ድርሰቶች ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳቸው እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እዚህ ላይ ከርእሶቹ ጀምሮ፣ ልዩ ትኩረትን ለ"እቁብ" እና "እቁብተኞች"፤ ለ"ማህበር" እና "ማህበርተኞች"፤ "እድር" እና "እድርተኞች"... መስጠት ማለት፣ በተለይም ጉዳዩን ከሥነሰብእና ሥነማህበረሰብ (ሶሺዮሎጂ፣ እና አንትሮፖሎጂ) አኳያ ለተመለከተው ማሞ ምን ያህል ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን እንደ ሕዝብና ማህበረሰብ እንቀጥል ዘንድ ዋልታና ካስማ በመሆን የያዙንን መሰረታዊያን በሚገባ እንደለዩዋቸው የሚያሳይ ነው። በተለይም፣ ከላይ በርእስ እና ርእሰ-ጉዳይነት ይዘው በስፋት የሄዱባቸው እነዚህ ሶስቱ ሰበነክ (ሂዩማኒስቲክ) ጉዳዮች አንዱን ከአንዱ መለየት በማይቻልበት ደረጃ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ምን ያህል የህልውናችን መሰረት እንደሆኑ፤ የአብሮነታችን ማሰሪያ ገመድ፤ ከሁሉም በላይ የአንድ ኢትዮጵያዊነታችን መለያ እንደሆኑ መገንዘብ የሚቻል ብቻ ሳይሆን፤ ማሞ ምን ያህል ከጊዜ ቀድሞ የማየት አቅም እንዳላቸው ሁሉ ያሳያልና ሰውየው የዋዛ አልነበሩም፤ ውለታቸውም እንደዛው።

በእነዚህ ሶስት ስራዎች ውስጥ አብሮነት በሚገባ ተንፀባርቋል። የመተጋገዝና መረዳዳት አስፈላጊነት ሊገባን በሚችል ሁኔታ ተብራርቷል፤ እቁብ ካለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አኳያ በራሱ መንገድ ተዘርዝሯል። ሀዘንን መካፈልና ሥነልቦናዊ ፈይዳው (በተለይ ለሀዘንተኛው) በቀላሉ የሚታይ አይደለምና የማሞ እነዚህን የማህበረሰብ ምሰሶዎች ቀድመው ማየታቸው፤ አይተውም በማህበረሰቡ ውስጥ ይሰርፁ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፉ ዘንድ ... በሶስቱና እራስ ራሳቸውን በቻሉ መጻሕፍት የሄዱበት ርቀት፣ በተለይ ዛሬ ላይ ሆኖ እነዚህ የማህበረሰብ ምሰሶዎች እየላሉ መሄዳቸውን ለተመለከተ የማሞ አስቀድሞ የማየት ችሎታን እንድናደንቅ ያደርጋልና ደራሲው በችሎታቸውም፤ በውለታቸውም ሊደነቁ ይገባል። (በተለይም እነዚህን ስራዎች ከአገርም ሆነ አገረ መንግሥት ግንባታ፤ ትውልድ ቀረፃ፤ እሴት ተከላ ... አኳያ ለተመለከታቸው ፋይዳቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም።)

ጉዳዩን መሰረት ለማስያዝ በማሰብ ወደ መስኩ ምሁራን ይዘነው ብቅ ብለን ነበር። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ (Urban Anthropology) ዶክትሬት (ፒኤች.ዲ) ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ ወደሚገኙትና በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የሶሺዮሎጂ መምህር ወደ ሆኑት አቶ ብሩክ ሽፈራው ዘንድ በመሄድ ጉዳዩን እንዲያብራሩልን ጠየቅናቸው። እሳቸውም፤

ደራሲ ማሞ ውድነህ ያነሷቸው ጉዳዮች እንደኛ ላለ ማህበረሰብ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች፣ ማህበራዊ ድርጅቶች (Social organizations) ናቸው። መንግሥትም ሆነ ሌሎች ተቋማት ለግለሰቡም ይሁን ለአካባቢው ማህበረሰብ በማይደርሱበት ሁኔታ ሁሉ የሚደርሱለት እነዚህ ተቋማት ናቸው። የሬሳ ሳጥን የሚገዛው እኮ እድር እንጂ መንግሥት አይደለም። እነዚህ ተቋማት ፋይዳቸው ብዙ ነው። አብሮነትን፣ መረዳዳትና መተሳሰብን፣ ሃሳብና መረጃ መለዋወጥን፣ ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበትን ወዘተ ብቻ ልንመለከት እንችል ይሆናል፤ ግን የእነዚህ ማህበራዊ ተቋማት ፋይዳ ከእነዚህም ያለፈ ነው። አጥፊን የመመለስ፣ የአባላትን ብልሹ አካሄድና ባህርይ (ካለ) የማረም፤ በችግር ጊዜ እርስ በእርስ ዋስ የመሆን፤ እርስ በእርስ የመተማመን መሰረቶች፤ ለክፉ ቀን ፈጥነው ደራሽ፤ የማህበራዊ ቁጥጥር (Social control) ተግባራትን የሚወጡ፤ የግጭት አፈታትም ሆነ መፍታት አቅማቸው ጠንካራ የሆኑ ... ተቋማት ናቸው። በመሆኑም በቀላሉ የሚታዩ ሳይሆኑ፣ መልካም ትውልድን ከመፍጠርና አገር ከመገንባት አኳያ ሁሉ ታይተው፣ ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ወሳኝ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊ ... ተቋማት ናቸው። በማለት ነበር የመለሱልን።

እዚህ ላይ እነዚህ ሶስቱን የማህበረሰብ አብሮነትንና የጋራ ህልውናን ከማፅናት አኳያ ጠበቅ አድርገን ያዝናቸው እንጂ ማሞ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የመጀመሪያዎቹ



**ደራሲና ጋዜጠኛ ማሞ ውድነህ**

አስር ስራዎች ቀጥሎ ያሉት ሌሎች አስሮቹም (የደቡብ ሱዳን ብጥብጥ፣ ብዕር እንደዋዛ፣ ሞንትጎመሪ፣ የኤርትራ ታሪክ፣ የኛው ሰው በደማስቆ፣ የ፪ ዓለም ሰላይ፣ ምጽአት-እሥራኤል፣ ሰላዩ ሬሳ፣ የ፲፯ቱ ቀን ጦርነት፣ እና የካይሮ ጆሮ ጠቢ) ማህበረሰብን ከማንቃት፣ ማስተማርና ማሳወቅ ላይ ያልተመሰረቱ አይደሉም። ይህ ደግሞ አንዱ የሥነጽሑፍ አላማ ነውና ማሞን ያስመሰግናቸዋል።

ከድርሰት ስራዎቻቸው ጎን ለጎን ስምንት ትያትሮችን ለመድረክ ያበቁት ማሞ ውድነህ በትርጉም ስራዎቻቸውም አንቱ የተባሉ ሲሆን፤ ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች፣ የስድስቱ ቀን ጦርነት፣ ሾተላዩ ሰላይ፣ የካይሮው ጆሮ ጠቢ ወዘተ እና ሌሎችም የተርጓሚነት ጥጋቸውን የሚያሳዩ ናቸው። በተለይ ምንም በሌለበት፣ በዚያ በ"ጨለማ ዘመን" የአገራቸው ሕዝብ፣ (በተለይ አንባቢው) በውጭው ዓለም ምን እየተደረገ እንደሆነ፣ የስልጣኔያቸው፣ የተንኮላቸው፣ የአኗኗራቸው ... ሁኔታ ምን እንደሚመስል እንዲረዳ፤ በአይነ ልቦናውም እንዲመለከት፤ በእግረ ልቦናውም ወደዚያው እንዲያመራ ምን ያህል በድርሰቶቻቸው ይለፉ እንደነበር የትርጉም ስራዎቻቸው ራሳቸው ይናገራሉ። በበርካቶች ዘንድም ማሞ ውድነህ ሳይታክትና በተከታታይ ጸሐፊነቱ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ አይን ገላጭ ነው መባላቸውንም እዚህ ሊነሳላቸው የግድ ይላል። (በነገራችን ላይ፣ የሊዮን ዩሪስ "ኤክሶደስ" ወደ አማርኛ ከመለሱ በኋላ ርእሱን በተመለከተ 300 ምሁራንን በ"ምን ልበለው?" ዙሪያ ማነጋገራቸውን፤ በመጨረሻም "ምጽአተ-እስራኤል" የሚለው ማለፉን ስንቶቻችን ነን የምናውቀው? ይህ ራሱ አንዱ የማሞ ልዩ መለያ ነውና አርአያነቱ የሚደነቅ ነው።)

ከእነዚህ ቀጥለው ያሉት 20ዎቹም (የበረሃው ተኩላ፣ ዘጠና ደቂቃ በኢንተቤ፣ ጊለን-የክፍለ ዘመኑ ሰላይ፣ የኦዲሣ ማኅደር፣ ከታተኞቹ፣ ከሕይወት በኋላ ሕይወት፣ ስለላና ሰላዮች፣ ምርጥ ምርጥ ሰላዮች፣ ዕቁብተኞቹ፣ አሉላ አባነጋ፣ የሰላዩ ካሜራ፣ ሰላይ ነኝ፣ በዘመናችን ከታወቁ ሰዎች፣ ዕድርተኞቹ፣ ሾተላዩ ሰላይ፣ ማኅበርተኞቹ፣ በረመዳን ዋዜማ፣ የበረሃው ማዕበል፣ ኬ.ጂ.ቢ.፣ ሲ.አይ.ኤና ጥልፍልፍ) ሲሆኑ፤ ሁሉም ከላይ የጠቀስነውን የደራሲውንና የሥነጽሑፍ ዓላማ የሳቱ አልነበሩም።

የወይዘሮ አልማዝ ገብሩ ባለቤት፣ የሶስት ሴቶችና የሶስት ወንዶች ልጆች አባት የሆኑት ማሞ በሰፋፊና ተንታኝ የጋዜጦች ላይ ጽሑፎቻቸውም ይታወቃሉ። በቀይ ባህር ጉዳይ፣ በግብፅና አጠቃላይ የአረቡ ዓለም ፖለቲካ፣ ስለ አፍሪካ ቀንድ፣ በሰሜኑ የአገራችን የተዛባ ታሪክ አረዳድ ዙሪያ፣ በወራሪ የውጭ መንግስታት ምክንያት በኢትዮጵያ በተካሄዱ ጦርነቶችና በኢትዮጵያ የድል የበላይነት መጠናቀቃቸውን ... በተመለከተ ሳያሰልሱ የጻፉ ቋሚ አምደኛ ነበሩና በዚህም ለአሁኑና ለመጪውም የመረጃ ምንጭ የሆኑ ስራዎችን ትተው ማለፋቸው ሌላው የባለውለታነታቸው ጥግና ገፅታ ነው።

መቼም ማሞ ጎልተው የሚታወቁበት ዋናው ዘርፍ ሥነጽሑፍ ነውና ስለ ባለውለታነታቸው ማረጋገጫዎቹ ከላይ የጠቀስናቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች በርካታ ስራዎቻቸውም (የበረሃው ተኩላ፣ ዘጠና ደቂቃ በኢንተቤ፣ ጊለን-የክፍለ ዘመኑ ሰላይ፣ የኦዲሣ ማኅደር፣ ከታተኞቹ፣ ከሕይወት በኋላ ሕይወት፣ ስለላና ሰላዮች፣ ምርጥ ምርጥ ሰላዮች፣ ዕቁብተኞቹ፣ አሉላ አባነጋ፣ የሰላዩ ካሜራ፣ ሰላይ ነኝ፣ በዘመናችን ከታወቁ ሰዎች፣ ዕድርተኞቹ፣ ሾተላዩ ሰላይ፣ ማኅበርተኞቹ፣ በረመዳን ውዜማ፣ የበረሃው ማዕበል፣ ኬ.ጂ.ቢ.፣ ሲ.አይ.ኤና ጥልፍልፍ ሲሆኑ፣ ዩፎስ-በሪራ ዲስኮች፣ መጭው ጊዜ፣ ዮሐንስ፣ የአሮጊት አውታታ፣ እኔና እኔ፣ ኤርትራና ኤርትራውያን፣ ሞት የመጨረሻ ነውን?፣ የደረስኩበት-፩፣ የደረስኩበት-፪፣ ....) ናቸውና ማሞ ከትውልዳቸውም ባለፈ ለመጪዎቹ ሁሉ የተረፉ ስለመሆናቸው፤ ስለ አገርና ወገን፤ ባህልና ታሪክ ... ስላላቸው አቋም አንባቢ ከስራዎቻቸው ሊገነዘብ ይችላል።

የካቲት ተወልደው የካቲት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ማሞን ልዩ ከሚያደርጓቸው ማንነቶች አንዱ የእድሜ ልክ ጸሐፊነታቸው ሲሆን፤ ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ሲጽፉ ኖረዋል። ይህም በራሱ የጥንካሬአቸው ማሳያ ነውና እውነትም ማሞ ብርቱ ነበሩ። (በነገራችን ላይ የካቲት ወር ካበረከተልን ፍሬዎች መካከል ሞገደኛው ብዕረኛ አቤ ጉበኛ፣ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር፣ ጸጋዬ ገብረመድህን፣ ማሞ ውድነህ .... እንደሚገኙ ያውቃሉ?)

የ'አምስት ዓይናው' ማሞ ውድነህ አስከሬን፣ እንደሳቸው በሥነጽሑፍ ምርታቸው፤ በታሪክ ተመራማሪነትና ተርጓሚነታቸው ... የባለውለታነት ማማውን በተቆጣጠሩት የአገር ባለውለታዎች፣ ከደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁና ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድኅን መካነ መቃብር አጠገብ ያረፈ ሲሆን፤ በተለይም የህብረተሰቡን "እጅ ይዘው" ወደ ንባብ በማስገባት በኩል የማሞ ውድነህ ስራዎች ተወዳዳሪ እንደ ሌላቸው በስራዎቻቸው ላይ ፍተሻን ያደረጉ ሲመሰክሩላቸው ይሰማልና ይህንንም ከስራዎቻቸው ጎን ለጎን እንደ አንድ አገራዊ ውለታ፤ ትውልድ የመገንባትና የመቅረፅ፤ አንባቢ ትውልድ የመፍጠር ሀላፊነታቸውን እንደተወጡ ያሳያል።

ህልፈተ ሕይወታቸው በተሰማ ሰሞን "ሶል" የተባሉ አድናቂያቸው "ንባብን የወደድኩት በእሳቸው የስለላ (espionage) መጻሕፍት ነበር። ምኑ ተጠቅሶ ያልቃል። ፊልድ ማርሻል ሮሜል በየበረሀው ተኩላ"፤ "የእኛ ሰው በደማስቆ"፤ "ሰላዩ ሬሳ" ... ኧረ ስንቱ፤ "ሳይላክ የቀረ ደብዳቤ" አይረሳኝም። እንዴ፣ ደብዳቤው ቢደርስስ ኖሮ? ማሞ በመጽሐፋቸው ፍፃሜአቸውን በአሳዛኝ አደረጉብን ያልናቸው ሁሉ ሮሜልን ሳላውቀው በመጽሐፉ ላይ አዝኜለት ነበር። አይ ልጅነት። አባታችን፣ ነፍሶን በገነት ያኑርልን።" በማለት ሀዘናቸውን መግለፃቸው ጎን ለጎን አንባቢ ትውልድ ከመፍጠር አኳያ የተወጡትን ሃላፊነት የመሰከሩላቸውን እዚህ በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል።

"ዲግሪ ያሳበደው፣ የስድስቱ ቀን ጦርነት፣ ካርቱም ሄዶ ቀረ፣ ጊለን የክፍለ ዘመኑ ሰላይ፣ ምጽአተ እስራኤል፣ የኛ ሰው በደማስቆ፣ የበረሐው ተኩላ፣ አሉላ አባ ነጋ፣ የካይሮው ጆሮ ጠቢ፣ ብዕር እንደዋዛ ... የተሰኙትን መጻሕፍት በእጅ ይዞ መታየት ምንኛ ክብር እንደነበረ ማን ይዘነጋል?" የሚለውንና በethiopianchurch.org ላይ ሰፍሮ የሚገኘውንም አስተያየት ከዚሁ ጋር በተያያዥነት ማንሳት ይቻላል።

ደራሲውና ጋዜጠኛው ሁለገብ በመሆናቸው የአክሱም ሐውልት አስመላሽ ኮሚቴ ውስጥ ከነፊታውራሪ አመዴ ለማ ጋር በመሆን ያገለገሉት፤ የዶጋሌ ጦርነት 100ኛ ዓመት መታሰቢያም ስለ ጀግናው አሉላ አባ ነጋ የፃፉትን ታሪካዊ መጽሐፍ ያበረከቱት፤ የዓድዋ ድል 116ኛ ዓመት በሚከበርበት ማለዳ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ፤ ለድርሰት ያላቸውን ልዩ ቦታ፣ ክብርና ፍቅር "ድርሰት የመጀመሪያ ሚስቴ (ባለቤቴ) ነች። ወይዘሮ አልማዝ ሁለተኛ ሚስቴ ነች" ብቻ ሳይሆን፤ "ሁለተኛዋ ባለቤቴ የመጀመሪያ ባለቤቴን አጥብቃ ነው የምትወዳት፤ የምታከብራትም" በሚለው ለየት ያለ አገላለፃቸውም ይታወቃሉ።

በመጨረሻም ማሞ ውድነህ ታመው አልጋ ላይ በዋሉበት ወቅት ጋሽ ስብሀት ገብረእግዚአብሔርም ታሞ ሆስፒታል ነበርና "... እኔም አሞኛል፤ አንተም አሞሀል። ሁለታችንንም እግዚአብሔር ይማረን . . ." በማለት የጻፈላቸው ደብዳቤ ሳይደርሳቸው ሁለቱም ማረፋቸውን በወቅቱ ጥበቡ በለጠ መዘገቡን ጠቅሰን እንሰናበት።

# ስፖርት

## የፍልሚያ ስፖርቶች የተመሰገኑበት የእድሜ ተገቢነት ጉዳይ

ቦጋለ አበበ

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ባለፈው እሁድ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስቴድየም በደማቅ የመክፈቻ ስነስርአት ተጀምሯል። ከትናንት በስቲያ አንስቶም የኦሊምፒክ በሆኑና ባልሆኑ በርካታ የስፖርት አይነቶች የተለያዩ ውድድሮች በፉክክር ታጅበው ቀጥለዋል። በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜዎች በታዳጊና ወጣቶች ላይ ትኩረት አድርገው በሚካሄዱ ውድድሮች የእድሜ ማጭበርበር ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑ ይታወቃል።

ይህ የወጣቶች ኦሊምፒክ ሲካሄድ በእድሜ ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ባይቻል እንኳን ችግሮችን በተቻለ መጠን ቀንሶ አገርን በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች የሚወክሉ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት ታስቦ ነው። በኦሊምፒኩ ባለፉት ሁለት ቀናት ውሎ ከእድሜ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ስፖርቶች ጎልተው የወጡ ችግሮች ባይኖሩም ሊበረታቱ የሚገቡ መልካም ጅምሮች እንደነበሩ መታዘብ ተችሏል። በተለይም እንደ ካራቴ በመሳሰሉ የፍልሚያ ስፖርቶች ተሳታፊዎች ያቀረቧቸው ወጣት ስፖርተኞች "አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል" እንደሚባለው የእድሜ ተገቢነት የሚነሳባቸው ሆነው አልተገኙም። ይልቁንም በነዚህ ስፖርቶች እየተወዳደሩ የሚገኙ ወጣቶችም ይሁኑ እንዲሳተፉ መርጠው ወደ ውድድሩ ስፍራ ያመጧቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በእድሜ ጉዳይ ላይ ያደረጉት ጥንቃቄ አስመስግኗቸዋል።

እንዲህ በተገቢው እድሜ ስፖርተኞች ፉክክር ሲያደርጉ ማየት ከዚህ ቀደም በመላ አገሪቱ ምንያህል ታዳጊና ወጣት ስፖርተኞች ሽልማትና ዋንጫን አልመው



በካራቴ ስፖርት የታዩት ወጣት ተወዳዳሪዎች በእድሜ ተገቢነት ጉዳይ ተመስግነዋል፣

በሚሰሩ ሰዎች እንደተዋጡና እንደተበደሉ የሚያሳይ ቁጭትን ይፈጥራል። ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው የወጣቶች ኦሊምፒክ መመስገን ካለበት ዋነኛ ጉዳይ በተለይም ትኩረት በማይሰጣቸው እንደ ካራቴ በመሳሰሉ የፍልሚያ ስፖርቶች ኢትዮጵያ ወደ ፊት ተስፋ ያላቸው በርካታ ባለተሰጥኦ ታዳጊዎች እንዳሏት ማሳየት መቻሉ ነው።

የዘወትር የስፖርቱ ነቀርሳ የሆነው የእድሜ ማጭበርበር ጉዳይ ከፍልሚያ ስፖርቶች በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውጤታማ በሆነችባቸው ስፖርቶች ክልሎች ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ ትምህርት እንደሚሆንም በውድድሮች ላይ የተገኙ የስፖርት ቤተሰቦች አስተያየት ሲሰነዝሩና ሲወያዩ ቆይተዋል።

በፍልሚያ ስፖርቶች በተለይም ትናንት በርካታ ፉክክሮችንባስተናገደውናካለፈውቶኪዮ2020ኦሊምፒክ ጀምሮ የኦሊምፒክ ስፖርቶች ውስጥ የተካተተው የካራቴ ስፖርት ላይ የታዩ ተወዳዳሪዎች በተገቢው እድሜ ለውድድር የቀረቡ ብቻም ሳይሆን በስፖርቱ ትልቅ አቅም ያላቸው መሆኑን አሳይተዋል። ስፖርቱ በኦሊምፒክ የተካተተ መሆኑም ለእነዚህ ተወዳዳሪዎች ትልቅ የሞራል ስንቅ እንደሰጣቸው በስፍራው ያነጋገርናቸው ወጣት ስፖርተኞችና ባለሙያዎች ተናግረዋል። በዚህ ስፖርት እነዚህን ባለተሰጥኦ ሊጋ ወጣቶች ትኩረት ሰጥቶ በቅርበት መከታተል ከተቻለም በቀጣይ በግብጽ በሚካሄደው የአፍሪካ ወጣቶች ቻምፒዮናና በሴኔጋል ዳካር በሚካሄደው የአለም ወጣቶች ኦሊምፒክ ውድድር ላይ ለአገራቸው አንድ አዲስ ነገር ማበርከት የሚችሉበት እድል እንደሚኖር ተስፋ አሳይተዋል።

ባለፈው የቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት በአትሌት ሰለሞን ቱፋ መወከል መቻሏ ከተለመደው የአትሌቲክስ ስፖርት ባሻገር በፍልሚያ ስፖርቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ከተቻለ ቢያንስ ተሳትፎ ከባድ እንደማይሆን ማየት ተችሏል። የካራቴ ስፖርትም በኦሊምፒክ መካተት መቻሉ አሁን በኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክ ብቅ ያሉት ታዳጊና ወጣት ስፖርተኞች ህልማቸው እስከ ኦሊምፒክ እንዲዘልቅ አድርጓቸዋል። እነዚህን ወጣቶች ደግፎና ተንከባክቦ የመያዝና በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ልምድ እያገኙ እንዲዳብሩ የማድረግ የቤት ስራው የብሔራዊ ፌዴሬሽኑና የኦሊምፒክ ኮሚቴ ይሆናል።

ከፍልሚያ ስፖርቶች አንዱ የሆነው ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ ዳዊት አስፋው፣ በዚህ የወጣቶች ኦሊምፒክ የእድሜ ጉዳይ ላይ ተሳታፊ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ቀደም ተብሎ ማሳሰቢያ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ። ያም ሆኖ በአንዳንድ ውድድሮች ሙሉ በሙሉ ችግር አይኖርም የሚል እምነት የላቸውም። "እድሜ ማጭበርበር የኢትዮጵያን ስፖርት ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም ብለን ተነጋግረን ተማምነናል" ያሉት አቶ ዳዊት ተሳታፊ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችም በዚህ ረገድ የተቻላቸውን ጥረት በማድረግ ኮሚቴውን እንደረዱት አብራርተዋል። ይህ የመጀመሪያ ወጣቶች ኦሊምፒክ እንደመሆኑም ከእድሜ ጋር የሚነሱ ችግሮችን በቀጣይ መሰል ውድድሮች ከባለሙያዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የተሻለ ውጤት የሚታይበት ልምድ እየተገኘ እንደሚገኝም አቶ ዳዊት ገልጸዋል።

## በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ምድብ ወንጀል ችሎት

ከሳሽ ጠቅላይ ኢቃቤ ህግ

ተከሳሾች፡-

1ኛ ካሊድ ራጎ ጠቀቶ
9ኛ ጋየ ደንቢ ገታ
10ኛ ደንበላ አየለ ጨቢሳ
11ኛ ሃቢብ አደም ከድር
12ኛ ፉአድ ሃሰን በሽር
13ኛ ኤዳሶ (ሚልኬሶ) ኑራ አገቶ
14ኛ ዳንኤል ከበደ ወርቁ
15ኛ ብርሃኑ ተሾመ ዎጌ
16ኛ ቦንሳ አራርሶ በኩያ
17ኛ ዳዊት ከድር በሌላ
18ኛ ደስታ አቢቾ ገነሞ
19ኛ ሳፋዬ ገነሞ በሪሶ
20ኛ ወንዲ በቀለ አሸናፊ
21ኛ መሀመድ አማን ቶላ
22ኛ አወል በዳሶ ሚሎ
23ኛ ገመዳ ገመቹ ኢደአ
24ኛ አቢና ኢደአ ጎበና
25ኛ አማን ደስታ ቴፎ
26ኛ ሲራጅ አብዱራህማን ዴኮ
27ኛ ሱልጢ ሱቢ ዋኮ
28ኛ አብደታ ታጁዲን አወል
29ኛ አብዱራማን ከድር ሁሴን
30ኛ አብዱራህማን ኮሮንቶ ጅሎ
31ኛ አደም ሁሴን ቦሩ
32ኛ አዶ መሃመድ ቡሳዋ
33ኛ ቦንሳ በዳሶ ገመዳ
34ኛ ዳውድ ሮጊቻ ዱባ
35ኛ ደስታ ከተማ ሙበረቱ
36ኛ ዱክቲያ ዱባ ሁቃ
37ኛ ገልቹ ተስፋዬ ሲቡ
38ኛ ገመቹ አናጂ ሀ/ሱሰን
39ኛ ገመቹ ዴኬ አኖሌ
40ኛ ጉተማ ሞጎሬ አራሮ
41ኛ ሃጂ ደዴቻ ሚኤሶ
42ኛ ሃለከኖ ዋሪዮ አብቱና
43ኛ ጃርሶ አዶሌ ጀልዴሳ
44ኛ ከድር በዳሶ ቁፋ
45ኛ ሎኮ ቂልጣ ወቲቻ
46ኛ ሎሎ አሰፋ ዱጎ
47ኛ መላኩ አስፋው ከቶ
48ኛ መሪጌታ ታደሰ ፈረደ
49ኛ ረመዳን ዴከማ ደንቢ
50ኛ ሮቤ ሂርበዬ ዱከሌ
51ኛ ሽምሱ መሀማድ ባንታ
52ኛ ሲራጀ ሳፋዬ ዋሬ
53ኛ ቶላ ከድር ሴሮ
54ኛ ቶሎሳ ገመዶ ኡሊ
55ኛ ኡስማን ባንካ በከሩ
56ኛ ዮሀንስ ቤሬ ቦረማ
57ኛ ባዲሳ ዋቆ ገሊጋሎ
58ኛ በላቸው ማሩ ገበየሁ
59ኛ ቡሾ ፈረደ ደቻሳ
60ኛ ደሜ ከተማ ሙዳ
61ኛ ጀሚላ ጊዘሊ ሙሳ
62ኛ ካሚላ አማን ጃርሱ
63ኛ ሳምሶን ሙሉጌታ
64ኛ አብዲ ቶሼ ሙመያሆ
65ኛ በላይ ንጉሴ ጊቴቲ
66ኛ ሃሰን አሊ ኢሳቅ
67ኛ ሲራጅ ገናሌ ሀላኬ
68ኛ አብደላ ሁሴን ሬባ
69ኛ ሎሜ ከርላ ዳሉ
70ኛ ወሰን ተሾመ መኮንን
71ኛ ቻለው ማሞ ሀይሌ
72ኛ አዋኒ በቀለ አለሙ
73ኛ በቀለች አሎንጂ ኦልባኖ
74ኛ ቢኒያም ዎያ ሃምዳ
75ኛ አብዱላሂ አሎ ኢሳቅ
76ኛ ታሪኩ ቡኑቲ ባሪሶ
77ኛ አብዱላዚዝ አብዶ አ/ዲጋ
78ኛ ሄኖክ ብሩክ ሀ/ጎርጊስ
79ኛ አብዱልከሪም ከድር
80ኛ አበበ ዳዲ
81ኛ ከቻቱ ዋኮ ጂሎ
82ኛ ቡሌ ገላኖ ጂሎ
83ኛ ቢኒያም አብርሃ ገ/ዮሀንስ
84ኛ አለም ገ/ሄቲ
85ኛ ገብረዮሀንስ ማውጫ
86ኛ ቴዎድሮስ አናጋው ከበደ
87ኛ ሰብለ ተመስገን አስረስ
88ኛ አብነት ዮሀንስ ዎቲቻ
89ኛ አመንቲ ቶሎሳ
90ኛ ሃሊማ አደም መሃመድ
91ኛ ጀሚላ ሁሴን ጨኮ
92ኛ ቱሬ ኡራጎ በሪሶ
93ኛ የትምወርቅ ከበደ ቦጋለ
94ኛ ወርቁ ፍቅሬ አለባቸው
95ኛ ሄኖክ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ
96ኛ ኤቢሳ ኬና አራርሶ
97ኛ ጉሴሳ መውጫ
98ኛ መሀመድ አደም
99ኛ ሀቢብ ኑራ ለሙ

መካከል ስላለው የሙስና ወንጀል ክርክር ጉዳይ በተመለከተ ከላይ ስማቸው የተገለጸው ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው በቀጠሮው ቀን በ29/10/2014 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደቡብ ችሎት እንዲቀርቡ አዟል፡፡

በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ምድብ ወንጀል ችሎት